# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 025 መስከረም 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# "ኢሬቻ ጥላቻን በፍቅር፤ ቂምና ቁርሾን በይቅርታ በመሻር አንድነትንና ወንድማማችነትን የሚያጸና ነው"

- አቶ ኃይሉ አዱኛ
የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሞ ሕዝብ ኢሬቻን ሲያከብር ጥላቻን በፍቅር፤ ቂምና ቁርሾን በእርቅና ይቅርታ በመሻር አንድነቱንና ወንድማማችነቱን የሚያፀናበት መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ:: የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ አባገዳዎች ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት ዕሴቱን ጠብቆ በሰላም እንዲከበር ዝግጅት መደረጉ ተገልጿል::

የኦሮሚያ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ የዘንድሮውን የኢሬቻ በዓል አከባበር አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ኢሬቻ አንድነት፣ ወንድማማችነትና ፍቅር ጎልቶ የሚታይበት ክብረ በዓል ነው:: በመሆኑም የኦሮሞ ሕዝብ ኢሬቻን ሲያከብር ጥላቻን በፍቅር፤ ቂምና ቁርሾን በእርቅና ይቅርታ በመሻር አንድነቱንና ወንድማማችነቱን የሚያጸናበት ነው ብለዋል::

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት የእርቅና የይቅርታ በዓል ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ያለምንም የሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት በአንድነት የሚከበር ታላቅ የአደባባይ በዓል ነው ሲሉ ገልጸዋል::

"ኢሬቻ ጥላቻን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# "ኢሬቻን ለማክበር ከውጭ ሀገር የሚመጡ እንግዶችን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለማስተናገድ ተዘጋጅተናል"

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- መስከረም 26 ና 27 የሚከበረውን የኢሬቻን በዓል ለማክበር ከውጭ ሀገራት የሚመጡ እንግዶችን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለማስተናገድ መዘጋጀቱን የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ:: ኢሬቻ የተወሰነ አካላት የሚያከብሩትና የሚያስከብሩት ሳይሆን የሁሉም መሆኑን በመረዳት ሁሉም ህዝብ የድርሻውን ሊወጣ ይገባዋል ተብሏል::

"ከውጭ ኢሬቻን... ወደ ገጽ6 ዞሯል

# በአማራ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች በ430 ሚሊዮን ብር የድጋፍ እህል ሊገዛ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በዝናብ እጥረት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች መንግሥት 430 ሚሊዮን ብር መድቦ ድጋፍ እህል ለመግዛት መወሰኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ አስታወቁ።

ርዕሰ መስተዳድሩ በወቅታዊ ጉዳዮች ከአሚኮ ጋር በነበራቸው ቆይታ በክልሉ በስምንት ዞኖች እና በ39 ቀበሌዎች የዝናብ እጥረት በመከሰቱ ነዋሪዎች ተቸግረዋል ብለዋል።

ሕዝባችን ሲቸገር ቀድመን መድረስ አለብን ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ፤ የዝናብ እጥረት ያጋጠማቸውን

በአማራ ክልል... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ አረጋ ከበደ



አብርሃም በላይ (ዶ/ር)

# መከላከያ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ያስገነባቸውን ቤቶች ለአቅመ ደካሞች አስረከበ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- መከላከያ ሚኒስቴር በ 103 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ያስገነባቸውን የመኖሪያ ቤቶች ለአቅመ ደካማ ዜጎች አስረከበ።

የመከላከያ ሚኒስቴር 116ኛውን የሠራዊት ቀንን ምክንያት በማድረግ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ለአቅመ ደካሞች ያስገነባቸውን ቤቶች አስረከበ።

በቤት ርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር)፤ መከላከያ ሠራዊት

መከላከያ ከመቶ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









ወጣት ይሁነኝ መሀመድ

# የአዲስ አበባ ወጣት ለኢሬቻ በዓል የሰላም ዘብ በመሆን ይንቀሳቀሳል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- መስከረም 26 በአዲስ አበባ የሚከበረውን የኢሬቻ በዓልን ምክንያት በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣት የሰላም ዘብ ሆኖ በመንቀሳቀስ የአካባቢውን ደህንነት እንደሚያስጠብቅ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ማህበር ገለጸ።

የማህበሩ ዋና ፀሀፊ ወጣት ይሁነኝ መሀመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ በመጪው ቅዳሜ በአዲስ አበባ የሚከበረውን የኢሬቻ በዓልን ተከትሎ ወጣቱ የሰላም ዘብ ሆኖ ይንቀሳቀሳል። ከዚህ ቀደም የተሰሩ ሰፊ ሥራዎች ሰላምን በማስፈን ሂደቱ ላይ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ያስችላሉ።

በማህበሩ ስር ያሉ ወጣቶች በበዓሉ አከባበር ወቅት በርካታ ተግባራት የሚከውኑ ሲሆን በዓሉ በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ ይሠራሉ ሲል ወጣት ይሁነኝ ገልጿል።

ወጣት ይሁነኝ እንደገለጸው፤ የሰላምና ጸጥታ ጉዳይ በዕለቱ በሚሠራ ሥራ ብቻ ሳይሆን ከበዓሉ ቀን ቀድሞ በሚሠሩ ሥራዎች ላይም መሠረቱን የሚጥል ነው። ከዚህ አንፃር ማህበሩ በርካታ ተግባራትን ሲከውን ቆይቷል። እነዚህ ሥራዎች ውጤታማ የሚሆኑበት ሰፊ እድል አለ።

የአካባቢው ማህበረሰብ ሰላሙን ሊያደፈርሱ ስለሚችሉ ጉዳዮች መረጃ ካለው አስቀድሞ ለመዘጋጀትና በአላስፈላጊ ጉዳዮች ላይ እንዳይሳተፍ እንደሚያደርገውም ወጣት ይሁነኝ ተናግሯል።

የማህበሩ ወጣቶች በመድረክ ላይም ይሁን በየአካባቢያቸው ሰላምን በሚመለከት ቀድመው የሚያውቋቸው ጉዳዮች እንዲሁም ተነሳሽነት ስላላቸው ከዚህ ቀደም በነበረው ልምድ በመውሰድ የሚሠሩ ቀሪ የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው ጠቅሷል።

ከወጣቱ በተጨማሪ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሰላምን ውድ ዋጋ በመረዳት ለአካባቢው ደህንነት ከፀጥታ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባውም አሳስቧል።

በአዲስ አበባና በሸገር ከተማ አማካይ በሚሆኑ ክፍለ ከተሞች የምክክር መድረኮች በመከወን ላይ መሆናቸውን ያመላከተው ኃላፊው፤ በዓሉን ለማክበር ለሚመጡ እንግዶች የሚጠበቅባቸውን በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለመስጠት ስለመዘጋጀታቸው ተናግሯል።

የከተማይቱ ወጣቶች ኢሬቻና መሰል በዓላት ላይ ሰላምን ከማስጠበቅ ጎን ለጎን የባህል ልውውጥ የመማማርን እድል የሚሰጥ መሆኑን በመገንዘብ እድሉን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ወጣት ይሁነኝ አሳስቧል።

# በመዲናዋ ለሚከበረው ኢሬቻ በዓል አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቀቀ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ቅዳሜ ለሚከበረው ኢሬቻ በዓል አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ መጠናቀቁን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ። የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል ማክበሪያ ሥፍራን የማጽዳት ሥራም በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል።

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የከተማ አስተዳደሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ የማክበሪያ ሥፍራውን ባጸዱበት ወቅቱ እንደተናገሩት፤ የኦሮሞ ህዝብ ለኢትዮጵያና ለዓለም ካበረከታቸው እሴቶች ውስጥ አንዱ የኢሬቻ በዓል ነው። በመዲናዋ በዓሉ የሚከበርበት ቦታ ውብና ጽዱ እንዲሆን የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዓሉን ለማክበር ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚመጡ እንግዶች ጽዱ በሆነ ቦታ ላይ እንዲያከብሩ አካባቢውን የማጽዳት ሥራ ተከናውኗል።

ይህ በዓል በአዲስ አበባ መከበሩ ቱሪዝምንና የሥራ እድልን አሳድጓል እንዲሁም ውበትንና ድምቀትን ፈጥሯል ያሉት አቶ ጥራቱ፤ ኢትዮጵያ ያሏትን እሴቶች በአንድነት፣ በፍቅርና በደስታ ማክበር ይገባል። ይህን ማድረግ ሀገሪቱ ለሚያጋጥሟት ችግሮች ሁሉ ቁልፍ ይሆናል ብዬ አምናለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

በዓሉን ለማክበር እና እንግዶችን ለመቀበል ከተማ አስተዳደሩ የሚጠበቅበትን ዝግጅት ሁሉ ማጠናቀቁን ገልጸው፤ እንኳን ለ2016 ዓመተ ምህረት የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ብለዋል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሙባሪክ ከማል በበኩላቸው፤ ኢሬቻ የገዳ ሥርዓት ካጎናጸፈን ትልቅ እሴቶች መካከል አንዱና መሠረታዊው በዓላችን ነው። ኢሬቻ የምስጋናና የአብሮነት፣ የይቅርታና የሰላም፣ የወንድማማችነት፣ የአንድነትና የፍቅር በዓል ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገበ ድንቅ ቅርሳችንም ነው ብለዋል።



ኢሬቻ ሲከበር ጎላ ብለው ከሚታዩ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ምስጋና ነው። በዚህም ፈጣሪ የማሳው ፍሬ በጎተራ እንዲገባ፣ የተራራቁ ዘመዶች እንዲገናኙ እና የበዓሉ ታዳሚ ከክረምት ወደ በጋ እንኳን ተሸጋገርኩ ብሎ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሙባሪክ ገለፃ፤ በአዲስ አበባ የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል የሚከበረው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነው። ክፍለ ከተማው በዓሉ በደመቀና በአማረ መልኩ እንዲከበር ህብረ ብሔራዊ ሁነቶችን ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት አከናውኗል። በዓሉ የሚከበርበትን አካባቢ የማሳመርና የማስዋብ ሥራ ተሠርቷል።

በጽዳት መርሐግብሩ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የከተማ አስተዳደሩ ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነን ጨምሮ የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም በጎፈቃደኛ ወጣቶች እና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ አባ ገዳዎችና ሀደ ስንቄዎች ተሳትፈዋል።

# የኢሬቻን በዓል በአንድነትና በሰላም ለማክበር መዘጋጀታቸውን ነዋሪዎች ገለጹ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል በአንድነትና በሰላማዊ መንገድ እንዲከበር አስፈላጊውን ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪ አቶ ቶሎሳ መርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ የሚከበረው ኢሬቻ ልዩ ሥነ ሥርዓት የሚከወነው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በመሆኑ የበዓሉ ማክበሪያ ሥፍራን የማጽዳት ሥራ ተከናውኗል። ይህ ቦታ ፈጣሪ የሚመሰገንበት በመሆኑ ቦታውን በልዩ ልዩ ባህላዊ ስልቶች የማስዋብ ሥራዎች ተሰርቷል።

በዚህም ህንፃዎች፣ አደባባዮች እና መሰል ቦታዎች በዓሉን እንዲመስሉ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል። በአሁኑ ሰዓት በዓሉ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሰዎች ሆኗል ያሉት አቶ ቶሎሳ፤ የኢሬቻ በዓል ከገዳ ሥርዓት የተገኘ የኢትዮጵያና የዓለም እሴት ነው ብለዋል።

ይህንን ቅርስ መጠበቅ አንድነትን፣ አብሮነትን፣ ወንድማማችነትን እና እህትማማችነትን ያጠናክራል ያሉት አቶ ቶሎሳ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች በብሔርና በሃይማኖት ሳይለያዩ አካባቢውን ሲያጸዱና ሲያስውቡ እንደቆዩ ተናግረዋል።

የለበስኩትም ልብስ የከንባታ ብሔረሰብ ልብስ ነው። ይህም በዓሉ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ትግስት ነዋይ በበኩላቸው፤ "የለበስኩት የጅማ ባህዊ ልብስ ነው" ብለው፤ በክፍለ ከተማው የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን በደማቅ ሁኔታ ለመቀበል የተለያዩ ቦታዎችን የማጽዳትና የማሳመር ሥራ ቀደም ብሎ መከናወን እንደጀመረ ገልጸዋል።

የኦሮሞ ህዝብ የሚታወቀው በእንግዳ ተቀባይነቱና በሰው አክባሪነቱ ነው። ይህ የሚገለጸው በምቹ፣ በውብና በማራኪ ቦታዎች አንድነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን በሚያንጽባርቁ ሁነቶች ነው። ይህንን ለማከናወን ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በቅንጅት እንደተሠራ ተናግረዋል።

በዚህም ህፃናት፣ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አባ ገዳዎች፣ ሀደ ስንቄዎችና የወረዳና የክፍለ ከተማ ከፍተኛ አመራሮች እንደተሳተፉም ጠቁመዋል።

"የኢሬቻ በዓልን ስናከብር የገዳ ሥርዓትን መሠረት በጠበቀ መልኩ በሰላማዊ መንገድ ማክበር ያስፈልጋል" ያሉት ደግሞ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ከምሱ ዴከማ ናቸው።

እንደ ወይዘሮ ከምሱ ገለፃ፤ በዓሉ አዲስ አይደለም። ለረጅም ጊዜ ሲከበር የቆየ ነው። ኢሬቻ በሀገርና በዓለም ደረጃ የታወቀ በዓል ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዜጎች በዓሉ ለማክበር ይመጣሉ። ስለዚህ በዓሉን በሰላማዊና በአንድነት ማክበር ያስፈልጋል ብለዋል።

በተያያዘም የበዓሉ አስተባባሪ ወጣት አበበ ደበሌ በበኩሉ፤ "በዓሉን የሚያከብሩ ሰዎች ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ በመሆኑ የበዓሉ ክዋኔ በሰላማዊ መንገድ እንዲከበር አስተባባሪ እንድሆን ተመርጫለሁ። ከዚህ በፊትም በዓሉ ደማቅ በሚያደርጉ የተለያዩ ሥራዎችን አግዣለሁ" ብሏል።

የዝግጅት ሥራው የተጀመረው ከአሥራ አምስት ቀን በፊት ነው። አሁን ደግሞ በዓሉን መሠረት ያደረጉ ጨዋታዎችና ክዋኔዎችን ለማከናወን እንደተዘጋጀ ገልጿል።



አቶ ቶሉሳ መርጋ



ትግስት ነዋይ



ወይዘሮ ከምሱ ዴከማ






ወጣት አበበ ደበሌ


# በዘንድሮ የኢሬቻ በዓል የቀረቡ የባህል አልባሳት በጥራትና በዲዛይን የተሻሉ ናቸው

**ሄለን ወንድምነው**


አባይነሽ መለሰ


አለምፀሐይ ለምለም


መለሰ መኮንን


ጫልቱ ቡቶ

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ የኢሬቻ በዓል ለገበያ የቀረቡ የባህል አልባሳትና ጌጣጌጦች በጥራት እንዲሁም በዲዛይን አቅርቦታቸው ካለፉት ዓመታት አንጻር የተሻሉ መሆናቸውን የባህል አልባሳት ሻጮችና ሸማቾች ገለጹ።

የባህል አልባሳት ነጋዴዎቹ ወይዘሮ አለምፀሐይ ለምለም እና አባይነሽ መለሰ በመጪው ቅዳሜና እሁድ ለሚከበረው የኢሬቻ በዓል ማድመቂያ የሚሆኑ ባህላዊ አልባሳትን ካለፉት ዓመታት በተሻሻለ ጥራት መቅረባቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

ባለፉት ዓመታት በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ባህላዊ አልባሳት ይቀርቡ እንደነበር አስታውሰው፤ በዘንድሮው ዓመት የባሌ፣ የወለጋ፣ የአርሲ፣ የጉጂ፣ የቦረና፣ የሸዋ እንዲሁም በተለያዩ የኦሮሞን አካባቢዎች የተለመዱ ባህላዊ አልባሳት በስፋት ለገበያ ማቅረባቸውን ተናግረዋል።

የሁሉንም አካባቢ ባህል ያማከሉ አልባሳት በብዛት ከመቅረባቸው በተጨማሪም በጥራት እና በዲዛይን አማራጮቻቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ አልባሳትና ጌጣጌጦች በመኖራቸው ሸማቾች ግብይት እየፈጸሙ መሆኑን አስታውቀዋል።

የባህል አልባሳቱ ዋጋ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ብዙ ጭማሪ እንዳላሳየ የጠቆሙት ነጋዴዎቹ፤ አልባሳቱ ባህላዊ ይዘታቸውን በጠበቀ መልኩ በሸማኔ እንዲሁም በአልባሳት ባለሙያዎች ተዘጋጅተው መቅረባቸውን አመላክተዋል።

ቀለል ያሉት የወንዶች ባህላዊ ሸሚዞች ከ500 እስከ 800 ብር ለገበያ መቅረባቸውን አስረድረተው፤ የሴቶች ሙሉ አልባሳት ደግሞ ከአንድ ሺህ እስከ አንድ ሺህ 500 ብር ለገበያ መዋላቸውን ተናግረዋል።

ለበዓሉ የሚቀርቡት አልባሳት የኦሮሞን ባህል አጉልተው ከማሳየታቸው በተጨማሪ የባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን ለምንሸጥ ነጋዴዎች ከፍተኛ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አስገኝተውልናል ብለዋል።

የባህል አልባሳትን ሲሸምቱ ያገኘናቸው አቶ መለሰ መኮንን እና ወይዘሮ ጫልቱ ቡቶ በበኩላቸው፤ ለዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ማድመቂያ የቀረቡት የባህል አልባሳትና ጌጣጌጦች በጥራትም በዲዛይን አማራጭም አስደሳች መሆናቸውን አስረድተዋል።

የባህል አልባሳት አቅርቦቱ ካለፉት ዓመታት የተሻሻለ ቢሆንም የዋጋው ጉዳይ ግን ነጋዴዎች እንደሚያቀርቡት ምክንያት ተመጣጣኝ ሳይሆን ከፍተኛ መሆኑን መታዘባቸውን ተናግረዋል።

ለኢሬቻ ማዲመቂያ የቀረቡት አልባሳትና ጌጣጌጦች የኦሮሞን ባህል መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ለበዓላት ስለምንጠቀምባቸው ለመግዛት ወስነናል ያሉት ሸማቾቹ፤ በቀጣይ የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ያገናዘቡ ዋጋዎች ቢቀርቡ በብዛት ለመገበያየት የሚቻልበት ፍላጎት ህብረተሰቡ ጋር መኖሩን ገልጸዋል።

በአንጻሩ ባህሉን ሳይለቁ በዘመናዊ መንገድ የተዘጋጁ አልባሳትና ጌጣጌጦች በስፋት መቅረባቸው ለበዓሉ ልዩ ድምቀት የሚሰጡ መሆናቸውንና ጥራት ላይ ትኩረት ያደረገው ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።


ለገበያ የቀረቡት ልብሶች በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን ያማከሉ መሆናቸውን የጠቆሙት ሸማቾቹ፤ ህጻናትም ሆኑ አዋቂዎች የሚፈልጉትን መርጠው መልበስ የሚችሉበት የበዓል አልባሳት መዘጋጀታቸው ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን አስረድተዋል።


ኢሬቻ የአደባባይ በዓል በመሆኑ በባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን በማጌጥ የኦሮሞን ባህል ለሌሎች ሀገራትና ለበዓሉ ታዳሚዎች ለማስተዋወቅ ዝግጅት ማድረጋቸውን ሸማቹች አስታውቀዋል፡፡


ወጣት ስምረት ብርሃኔ


ወጣት ስሜነሽ ወብዓለም

ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ


ወጣት ጫላ ተስፋዬ


ወጣት ነጋሳ ታድላ

# "ኢሬቻ ባህላዊ ዕሴቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፉ ኃላፊነት የእኛ የወጣቶች ነው"

\- የአዲስ አበባና ሸገር ከተማ ወጣቶች

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓልን ባህላዊ ዕሴት አስጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፉ ኃላፊነት የተጣለው በወጣቶች ላይ ነው ሲሉ የአዲስ አበባና ሸገር ከተማ ወጣቶች ገለጹ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣት ስምረት ብርሃኔ እና ወጣት ስሜነሽ ውብዓለም የኢሬቻ በዓል ባህላዊ ዕሴቱን ጠብቆ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፍ ኃላፊነት አለብን ሲሉ ሃሳባቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

በዓሉ በተሳካ ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንዲከበር የበኩላችንን ሚና እንወጣለን ያሉት ወጣቶቹ፤ ኢሬቻ የሰላምና የፍቅር በዓል መሆኑን በአግባቡ የምናሳይበት አጋጣሚ ነው ብለዋል።

ባለፈው ዓመት የኢሬቻን በዓል በድምቀት እንዳከበሩ አስታውሰው፤ የዘንደሮውንም ከባለፈው ዓመት አስበልጠው በድምቀት ለማክበር ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የ2016 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን በድምቀት ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ሰፊ ዝግጅት ማድረጋቸውን ገልጸው፤ የአንድነት፣ የአብሮነት፣ የእንግዳ ተቀባይነት እንዲሁም የይቅርታ መገለጫ የሆነውን በዓል ለማክበር የሚመጡ እንግዶች እንደቤታቸው እንዲሰማቸው አድርገን እንቀበላቸዋለን ሲሉ ተናግረዋል።

በዓሉን ለመታደም የሚመጡ እንግዶችን በአምስቱም የመግቢያ በሮች በመቀበል የማረፊያና የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰብ አባላት የበዓሉን ባህላዊ እሴት በተግባር በማሳየት በድምቀት ቢያከብሩ አንድነቱን ይበልጥ ማጠናከር እንደሚቻል አመላክተዋል።

በዓሉን በዲምቀት ከማክበር እና እንግዶችን ከመቀበል ባለፈ በዓሉ እሴቱን ጠብቆ እንዳይከበር ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አካላትን የመከላከልና በሕግ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ እንደሚሰሩ አስገንዝበዋል፡፡

የሸገር ከተማ ነዋሪዎቹ ወጣት ጫላ ተስፋዬ እና ነጋሳ ታድላ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ ከክረምት ወደአደይ ወቅት ለአሸጋገረን ፈጣሪ ምስጋና የምናቀርብበት፣ በክረምቱ ዝናብና በወንዞች መሙላት ምክንያት ተራርቆ የቆየ ሰው የሚገናኝበት እንዲሁም የመልካም ምኞት መግለጫ በዓል ነው ብለዋል፡፡

ኢሬቻ የኦሮሞን ባህል ለሌሎች ሀገራት የምናስተዋውቅበትና አንድነትን የምናጠናክርበት በዓል በመሆኑ የበዓሉን እሴት አስጠብቀን ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፉን ኃላፊነት እንወጣለን ሲሉ ተናግረዋል።

ኢሬቻ ከሌሎች ወንድሞቻችን ጋር የምንተዋወቅበት በዓል ነው ያሉት ወጣቶቹ፤ ልዩነትን በማጥበብ አንዱ የአንዱን ባህል በማክበርና በመጠበቅ ሠላማዊ በሆነ መንገድ ባህላዊ እሴቱን አስጠብቀን ማክበር ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ትውልዱ ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ወቅቱን የዋጀና በተግባር የተደገፈ ሥራ ሊያከናውን እንደሚገባም ወጣቱቹ ገልጸዋል።

# ድሬዳዋን ወክለው የኢሬቻ በዓልን የሚታደሙ ልዑካን ዛሬ አዲስ አበባ ይገባሉ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ድሬዳዋን ወክለው የኢሬቻ በዓልን የሚታደሙ ልዑካን ዛሬ አዲስ አበባ እንደሚገቡ የድሬዳዋ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሚካኤል እንዳለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደ ኢሬቻ አይነት በዓላት ከአንድ አካባቢ ወጥተው ሀገራዊ ቅርጽ ሲይዙ እንደ ሀገር የተጀመሩ አብሮነትና አንድነትን የሚያጠናክሩ ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡ በዚህም መስከረም 26 እና 27 የሚከበረውን የኢሬቻ በዓል ላይ ለመታደም ከተማዋን የሚወክል ቡድን በዛሬው ዕለት ወደ አዲስ አበባ የሚገባ ይሆናል፡፡

ልዑካን ቡድኑ 50 ከሚጠጉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎች፣ ሴቶች እና ወጣቶች የተውጣጣ ነው ያሉት አቶ ሚካኤል በተጨማሪም ከከተማዋ በግላቸው በዓሉ ላይ ለመታደም የሚመጡ ሰዎች ይኖራሉ ብለዋል፡፡

በዚህም የሚታዩ ጥላቻዎችን በማስወገድ በቀጣይ ሁሉም ኢትዮጵያውዊ በአንድነት ሚያከብረው ይሆናል ያሉት አቶ ሚካኤል፤ ኢሬቻ ለሰላም፣ ለአንድነት እና ለዜጎች መቀራረብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ልዑካኑ ጥሩ ጊዜን አሳልፈው እንደሚመለሱ ተስፋ አለን ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሚካኤል ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩን ወክሎ የሚመጣው ልዑካን ቡድን ከተለያዩ ብሄር ብሄረሰብ አልባሳት አሸብርቀው በዓሉ ላይ የሚሳተፍ ይሆናል፡፡ በተለይም የድሬዳዋን ባህላዊ ቁሳቁሶችን እና የቱሪዝም ቦታዎችን የሚገልጹ አልባሳት በስፋት በማንጸባረቅ የበዓሉ አንድ ድምቀት ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

አቶ ሚካኤል አክለውም፤ የኢሬቻ በዓል አሁን ያለውን ባህላዊ እሴቱን እንደጠበቀ በዩኔስኮ የማስመዝገብ እና ለቱሪዝም ዘርፉ የገቢ ምንጭ ለማድረግ መሠራት አለበት ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ዘንድሮ መስከረም 26 እና 27 ለሚከበረው በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው፤ በዓሉም በሰላም እና በአንድነት እንዲከበር ሁሉም ህብረተሰብ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓላቱ የባህላዊ እሴቶቻችን ታላላቅ መገለጫዎች ናቸው!

የአንድ ሀገር ሕዝቦች እውነተኛ ብሄራዊ ማንነት የሚገነባው በዛች ሀገር ባሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ድምር ውጤት ነው። እነዚህ እሴቶች ዘመናትን እየዋጁ እና በዘመናት እየተዋጁ ትውልዶች ከትናንት ዛሬ ፤ ከዛሬ ደግሞ ነገ የተሻሉ ቀናትን ተስፋ አድርገው መኖር እንዲችሉ ዋነኛ አቅም ሆነው ያገለግላሉ።

በተለይም ባለንበት ዘመን እነዚህ እሴቶች የአንድን ማኅበረሰብ ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት ሂደት ውስጥ ካላቸው አስተዋጽኦ አንጻር ከፍ ያለ ትኩረት እየተሰጣቸው ይገኛል። እሴቶቹ ከባለቤቱ ማኅበረሰቡ አልፈው ዓለም አቀፍ እውቅና የሚያገኙበት እና አግባብ ባለው መንገድ የሚጠበቁበት አስቻይ ሁኔታም በስፋት እየተስተዋለ ነው።

ኢትዮጵያም እንደ ሀገር የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ከመሆን ባለፈ የብዙ ሺ ዓመታት የሀገረ መንግሥት ታሪክ ባለቤት በመሆኗ፤ ለሀገሪቱ ሕዝቦች የተሻሉ ነገዎችን መፍጠር የሚያስችሉ ብዛት ያላቸው ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ባለቤት ነች። እነዚህ እሴቶች እንደ ሀገር እስከዛሬ ለመጣችባቸው ረጅም የታሪክ ምዕራፎችም ዋነኛ አቅም ናቸው።

እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ከራሱ አልፎ ከሌሎች ጋር በሰላም ፣ በፍቅር እና በአንድነት መኖር የሚያስችሉ በየራሳቸው ምሉዕ የሆኑ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች አሉት። ከትናንት ዛሬ ራሱን ሆኖ መኖር የቻለው እነዚህ እሴቶቹ በሰጡት አቅም እና በገነቡበት ማንነት ነው። በቀጣይም ከራሱ ጋር ተስማምቶ የተሻሉ ነገዎቹን መፍጠር የሚችለው በነዚሁ እሴቶቹ እየተደገፈ እንደሆነም ይታመናል።

የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱንና እንደሚያስተምሩን ፤ እንደ ማኅበረሰብ ነገን ብሩህ አድርጎ ለማሰብ ከሁሉም በፊት ከራስ ጋር መታረቅ ያስፈልጋል፤ ከዚህ የተነሳም በየትኛውም ሁኔታ ከራሱ ጋር የተጣላ/ ከማንነቱ ጋር ያልተስማማ / ማኅበረሰብ የተሻሉ ነገዎችን መፍጠር አይችልም። እነዚህን ቀናት ለመፍጠር የሚያደርጋቸው ያልተሳኩ ጥረቶችም የከፋ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ የሚያስገኙለት ፋይዳ የለም።

እነዚህ እሴቶች ለሰው ልጅ ተለዋዋጭ የውስጥ ፍላጎቶች በሂደት ተገዥ የሚሆኑ ፤ ዘመንን እየተዋጁና በዘመን እየተዋጁ የሚሄዱ ፤ በዚህም በራሳቸው የትውልዶችን የመሆን መሻት የማስተናገድ አቅም ባለቤት በመሆናቸው በየትኛውም መልኩ እነሱን ተቀብሎ ማስተናገድ ተፈጥሯዊ ሂደታቸውን ለተሻለ ተጠቃሚነት የማብቃት ያህል የሚቆጠርና የሚበረታታ ነው።

እኛም እንደ ሀገር ያሉንን ብሔር ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ተቀብለን የአደባባይ እውቅና የመስጠታችን ሂደት ፤ አንድም እንደሀገር ፈተና ለሆነብን ሰላም የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍያለ ነው። ከዛም ባለፈ መገንባት ለምንፈልገው የጋራ ሀገራዊ ማንነት አልፋና ኦሜጋ እንደሚሆን ይታመናል።

እንደ ሀገር የክረምቱን መገባደድ ተከትሎ ያከበርነው የቡሄ በዓል ፤ መስከረም ከጠባ ያከበርናቸው፤ ብሄራዊውን ጨምሮ የተለያዩ ብር ፣ ብሔረሰቦች የዘመን መለወጫ እና የመስቀል በዓላት የማንነታችን እሴቶች ናቸው። ለነዚህ እሴቶች የምንሰጣቸው እውቅና በአንድም ይሁን በሌላ የብሄራዊ ማንነታችን አቅም እና ጥንካሬ ምንጭ ነው።

በሳምንቱ መጨረሻም የምናከብረው የኢሬቻ በዓልም ከፍ ያሉ ማኅበራዊ እሴቶች ያሉት፤ እንደ ሌሎች የሀገራችን ብሔር ፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ማኅበራዊ እሴቶች በብሄራዊ ማንነት ግንባታ ውስጥ ከፍ ያለ አበርክቶ ያለው ነው። የኢትዮጵያዊነት ሌላው ገጽታ ማሳያ ደማቅ ቀለም ፤ የአንድነቱ ማሰሪያ ጠንካራ ገመድ እንደሆነም ይታመናል።

የኢሬቻ በዓል ከክረምት ወደ መስከረም፣ ከጨለማ ወደ ፀሐይ መሸጋገሪያ ያለውን ብሩህ የዘመን ታሳቢ ተደርጎ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት፤ በቀደሙት ጊዜያት ተቀያይመው የነበሩ ሰዎች ይቅርታ የሚጠያየቁበት እና ይቅር የሚባባሉበት፣ በጋራ የሚያመሰግኑበት በዓልም ነው። ይህም ሀገራዊ ሰብአዊ እሴቶችን ለማጎልበት ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል።

እንደ ሀገርም ማኅበራዊ ትስስር በመፍጠር የሕዝቦች አንድነትን ለማጠናከር እንዲሁም የግጭት ማስወገጃ ዘዴ ሆኖ ማገልገል የሚችል፤ ከኦሮሞ ሕዝቦች ባሻገር ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን በአንድነት አቅፎ የሚያሳትፍ ነው። የበዓሉ እሴቶች ለጀመርነው ሀገራዊ ልማት ስኬት የሚኖረው ፋይዳም ከፍ ያለ ነው።

ይህንን ታሳቢ በማድረግ ስለ ኢሬቻም ሆነ መሰል በዓላት በማኅበረሰቡ ውስጥ ትክክለኛ ግንዛቤ በመፍጠር፤ ባህላዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀው ያለአንዳች የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት በሰላማዊ መንገድ የሚከበሩበትን ሥርዓት ማበጀት ፤ ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ያስፈልጋል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

ኢፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢሬቻ የሰላም በዓል ፤ በሰላም እንዲከበር

**ሰሚራ በርሀ**

አንድ ሰው ተወልዶ አድጎ ትልቅ ሰው ሆኗል ለመባል የልጅነት ፣ የአፍላነት እና የወጣትነት ጊዜያትን ያልፋል፤ በዚህ የህይወት ዑደት ውስጥ የዚህ ሰው አስተሳሰብ እና ማንነት በብዙ መንገድ ይቀያየራል፡፡ በዘመን በተተካ ቁጥርም ያለው አኗኗር ይቀየራል። በዚህ መሀል ግን ከዘመን ዘመን የማይለዋወጡ መንፈሳዊ ፣ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀው ከትውልድ ትውልድ የሚሻገሩ በዓላት አሉ። እነዚህ በዓላት በብዙዎች ዘንድ የአንድ ማኅበረሰብ ዋነኛ መገለጫም ተደርገው ይወሰዳሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከአኗኗራችን ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው ብዙ በዓላት ባለቤቶች ነን፡፡ ከነዚህ በዓላት ውስጥ በአደባባይ የምናከብራቸው ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የአደባባይ በዓላት መሠረታቸው ሃይማኖት ቢሆንም በውስጣቸው የተለያዩ እሴቶች አሏቸው።ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር ባህላዊ እሴቶችንም በማንጸባረቅ፣ታሪካዊም ይዘት ኖሮአቸው፣ በየዓመቱ በድምቀት ይከበራሉ፡፡በነዚህ በዓላት ላይ ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ክፍል ሁሉ ሳይቀር ከየአቅጣጫው ይሰባሰባሉ፡፡

እንዲህ ሕዝብን በማሳተፍ የሚከበሩ በዓላት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው መስቀል፣ የኦሮሞ ማኅበረሰብ በልዩ ሁኔታ የሚያከብረው ኢሬቻ ፣ ጊፋታ (የወይላይታ ዘመን መለወጫ) እና የያሆዴ (የሀዲያ የዘመን መለዋጫ) ጥቂቶቹ ናቸው። የመስቀል በዓልም ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ትውፊቱን ጠብቆ ከዓመት ዓመት ይከበራል። በተለይም በመስቀል ዋዜማ የሚከበረው ደመራ በእምነቱ ተከታዮች ልዩ ስፍራ አለው፡፡ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት/ ዩኔስኮ/ ከማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ የተመዘገበ ትልቅ በዓል ነው፡፡

እነዚህን በዓላት ባህላዊና መንፈሳዊ ይዘታቸውን እንደያዙ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ አሁን ላይ ደርሰዋል። ካላቸው መንፈሳዊና ባህላዊ ክዋኔ የተነሳም ከእምነቱ ተከታይ አልያም ከአካባቢው ማኅበረሰብ ውጪ የሌሎችን ኢትዮጵያውያንና የውጭ ሀገር ዜጎችን ቀልብ በመሳብም በኩል ትልቅ ሚና አላቸውና እነዚህ ቱሪስቶችም ዓመት ጠብቀው ሀገራችን እንዲመጡ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራሉ።

የበዓላቱን ታሪካዊ ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን በጠበቀ መልኩ በየዓመቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚጠይቀው ሥራ ወይም ዝግጅት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለይም ይዘታቸውን ጠብቀው መከበራቸው ከሁሉ በላይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ በዓላቱ የአብሮነት ፣የብዝሃነትና የወንድማማችነት መገለጫ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በተለያየ እምነት ፣ የባህል ልዩነት ያላቸው ወጣቶች በዓላቱ የሚከበሩባቸውን አካባቢዎች በጋራ በማፅዳት ለበዓላቱ አከባባር ያላቸውን አጋርነት ሲገልጡ ማየት እየተለመደ መጥቷል። ይህም ከተለያየ ቤተሰብ የተገኘን ፣ የራሳችን እምነት እና ባህል ያለን ብንሆንም በመከባበር እና በተቀራረበ የአብሮነት መንፈስ ያደግን ጥሩ ጉርብትና ያለን ሕዝቦች መሆናችንን ያሳያል፡፡

እንዲህ ያለው የመተባበርና የመከባበር መንፈስ በዓሉን ለሚያከብር ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ከውጪ ሆኖ ለሚመለከትም ትልቅ መልእክት በማስተላለፍ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ በዓሉ ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን በተለያየ መልኩ ጥረት የሚያደርጉ ወጣቶች እና በጎ ፍቃደኞች፣ ፕሮግራሙ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በተለያየ መንገድ የሚሳተፉ አስተባባሪዎች የበዓሉ ተሳፊዎች እና የፀጥታ አካላት ቅንጅትና ተናቦ መስራት ለበዓላቱ አከባበር ስኬታማነት ትልቅ አቅምም ነው፡፡

እንደ ቀደሙት ወቅቶች ሁሉ የእነዚህ ሁሉ አካላት ትብበር እና መናበብ ታክሎበት የመውሊድና የመስቀል ደመራ በዓላት ያላቸውን ታሪክ ፣ ባህል እና ሃይማኖታዊ ትውፊት ይዘው በሰላም እና በድምቀት ተከብረዋል። ለዚህም የበዓሉ ባለቤት የሆነው መላው ሕዝባችን ትልቁን ድርሻ ወስዷል። ምስጋናም ሊቸረው ይገባል፡፡

በርግጥ ሀገራት በጊዜ ሂደት የተለያዩ ፖሊሲዎችን ይከተላሉ ያሻሽላሉ፡፡ በዚህ መሃል የሕዝባቸውን አኗኗር የሚቀይሩ እና የሚያቀሉ ከዓለም ጋር እኩል የሚያስኬዱ ሥርዓቶችን ይዘረጋሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም እንደ ሀገር ልዩ የሚያደርጋቸውን ባህላዊ፣ ማኅበራዊና መንፈሳዊ እሴቶችን አጉልተው ለማሳየት ይጥራሉ። ይህ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ነው።

እኛም እነዚህ በዓላት ከሀገራችን አልፈው ስማችንን በበጎም ሆነ በመጥፎ ለማስጠራት ያላቸውን አቅም በመረዳት ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ስናከብራቸው ቆይተናል። የእኛነታችን መገለጫ የሆነው የኢሬቻ በዓልም በተመሳሳይ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከበር የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ያሉትን አካላት ማገዝና ለሰላሙ ተባባሪ መሆን ይጠበቃል፡፡

ኢሬቻ የምስጋና በዓል ነው። "ኢሬቻ ማለት ዋቃ (ፈጣሪ) የፈጠረውን ማመስገን ማለት ነው" የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፤ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው ፈጣሪው /ዋቃ ምስጋናውን የሚያደርስበት በዓል ነው። ማኅበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ልዩነት ሳይፈጠር የኦሮሞ ሕዝብ ለዘመናት በጋራ ሲያከብር የቆየ ዛሬም እያከበረው ያለ በዓል ነው።

"ክረምት ለሊት ነው። ለሊት ደግሞ ጨለማ ነው። ጨለማ ለአውሬ እንጂ ለሰው ልጅ አይሆንም። ጨለማው ሲነጋ ደግሞ ብርሃን ነው፤ ብርሃን ሲሆን ሃሳብ የለም ደስታ ይሆናል። መስከረም ሲጠባ ማለት ይህ ነው" በማለት የኦሮሞ ሕዝብ ከክረምት መገባደድ በኋላ የኢሬቻ በዓልን ያከብራል።

በኢሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ሕዝብ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደኅንነት ፈጣሪውን ዋቃን ይለምናል፤ ያመሰግናል። "የተጣላ ታርቆ፣ ቂሙን ትቶ በነጻ ልቦና ፈጣሪ ንጹህ ወዳደረገው የውሃ አካል ይሄዳል። ኢሬቻ ቀልብ የሚነጻበት ቦታ ነው።

የኢሬቻ በዓልን ለማክበር የሚወጣ ታዳሚ እንደ ሳር ወይም አበባ ያለ እርጥብ ነገር በእጁ ይዞ መምጣት ይጠበቅበታል፤ ይህም “ፈጠሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው” የሚለውን ትልቅ መልእክት ለማስተላለፍ ነው።

በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተራራቀ የሚገናኝበት በመሆኑ ከጸብ ይልቅ ፍቅርን፣ ከጥላቻና ከመራራቅ ይልቅ አንድነትን በማጉላት ኢትዮጵያዊነታችንን ይበልጥ የምናጠናክርበትና የምናሳይበት ሊሆንም ይገባል፣

"እንኳን ሰው፤እቃ ከእቃ ይጋጫል" እንደሚባለው፤ አዎ! ሰው አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ ይጋጫል፣ እንደ ሕዝብም የማያግባቡን ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ዓይነት በዓላችን ላይ ከማያግባቡን ይልቅ በሚያስማሙን ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ፤ ችግራችንን ወደጎን ትተን በፍቅር በመተሳሰብና በይቅርታ በመተላለፍ በሰላም ማክበር ይጠበቅብናል፣አንዳንድ የእኩይ ተግባር ነጋዴዎች አብሮ የኖረን ሕዝብ ለማቃቃር በናፍቆት የሚጠብቃቸውን የአደባባይ በዓላቱን ለማደብዘዝ በጠቅላላው ኢትዮጵያዊ መገለጫዎቻችንን ለማኮሰስ ሊጥሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን እኛ አስተዋይ በመሆን ችግር ቸርቻሪዎችን ወደጎን ብለን፣በዓሉ በሰላም ይከበር ዘንድ የበኩላችንን መወጣት አለብን፣

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ደግሞ ያለፉት የመውሊድና የደመራ በዓላት ናቸው፣ የበዓሉ ታዳሚ በሰላም ወጥቶ በሰላም ወደቤቱ ለመመለሱ ትልቁን ድርሻ የያዘው እራሱ ታዳሚው ነው፡፡ኢሬቻም በሚከበርባቸው ሁለት ቀናት የበዓሉ ታዳሚዎችን ጨምሮ መላው ኢትዮጵያዊ አንድ በመሆን የጸጥታ ኃይሎችን በመደገፍ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

# ኢሬቻ የህብረብሔራዊነት እና ውበት መገለጫ ነው

**በኢፕድ ሪፖርተሮች**

አዲስ አበባ፡- የተስፋ፣ የሰላም፣ የፍቅር እና የውበት መገለጫ ተደርጎ የሚታሰበው የኢሬቻ በዓል ዋዜማ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ተከብሯል።

የተስፋ፣ የሰላም፣ የፍቅር እና የመልካም ምኞት መገለጫ ተደርጎ የሚታሰበው የኢሬቻ በዓል ዋዜማ "ኢሬቻ የአንድነትና የወንድማማችነት ዓርማ" በሚል መሪ ሃሳብ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እና በንፋስስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ተከብሯል።

የአቃቂ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር አበራ ብሩ በመርሃ ግሩ ላይ እንደገለጹት፤ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስጦታና ድል የሆነው የኢሬቻ በዓል በሰላም እንዲከበር ሀደ ሲንቄዎች፣ ቄሮና ቀሬ፣ አባገዳዎች፣ ፎሌዎች ሃላፊነታችሁን ልትወጡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል። የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት ተምሳሌትነቱን የምናሳይበት ጊዜ ነው ሲሉም ነው የተናገሩት።

አባገዳዎች በመርሃ ግብሩ መክፈቻ የክረምቱ ወራት አልፎ ወደ ብርሃን ወጥተናል ሲሉ አምላካቸውን አመስግነው፤ እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን በማለት መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የተስፋ፣ የሰላም፣ የፍቅር እና የመልካም ምኞት መገለጫ ተደርጎ የሚታሰበው የኢሬቻ በዓል ዋዜማ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ሁለገብ አዳራሽ በትናንትናው ዕለት ተከብሯል።

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሙሉነ ፈይሳ እንደተናገሩት፤ የኢሬቻ በዓል አብሮነትና አንድነት የሚጸናበት ነው።



እንደ አቶ ሙሉነ ገለጻ፤ በዓሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እሴት የሚጠናከርበት ነው ያሉ ሲሆን፤ ከብሔር ብሔረሰቦች ጋር በጋራ መከበሩ ሀገራዊ መግባባትን እንዲጎለበት ያግዛል።

አቶ ሙሉነ አክለውም፡-ኢሬቻ በክፍለ ከተማ ደረጃ መከበሩ በዓሉን ይበልጥ ለማስተዋወቅና የከተማውን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

በዓሉ የመረዳዳት ባህል ሚጠናከርበትና ውስብስብ ችግሮች የሚፈቱበት ነው ያሉት አቶ ሙሉነ፤ በጋራ አብሮ የማደግና የመበልጸግ እሴት ያለው በዓል እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢሬቻ የሰው ልጆች እኩልነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት በባህላዊ መንገድ የሚፈጸምበት በመሆኑ በተለይ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበትን ውስብስብ ችግሮች ለማስወገድ እንደ ኢሬቻ ያሉ ባህላዊ እሴቶችን ማጠናከር እንደሚገባም ነው አቶ ሙሉነ የጠቆሙት።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የኢሬቻ ቅድመ ዝግጅት በዓል ሳምንት መርሃ ግብር በትናንትናው ዕለት ሲከበር በመርሀግብሩ ላይ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ንጋቱ ዳኛቸው ባስተላለፉት መልዕክት፤ ኢሬቻ ሲከበር ፍቅር ሰላም ይቅርታና መተዛዘንን በማስቀደም ሊሆን ይገባዋል።

ኢሬቻ የገዳ ሥርዓት መገለጫ የአንድነት፣ የወንድማማችነትና የእህታማማችነት ምልክት የህብረ-ብሔራዊ አብሮነትና ውበት መገለጫ ነው ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ እሬቻ የዓለም ሀብት እና የቱሪዝም መስህብ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል።

## መከላከያ ከመቶ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ከህዝብ የወጣ ለህዝብ የሚኖር ሠራዊት በመሆኑ ህዝብን ከመጠበቅ ባለፈ የአቅመ ደካሞችን የቤት ችግር ለመቅረፍ አጋርነቱን ማሳየቱን ገልጸዋል።

ሠራዊቱ የሀገርን ዳር ድንበር ከማስጠበቅ ባሻገር ከደመወዙ በመቀነስ አቅመ ደካሞችን በመደገፍ ህዝባዊነቱን እያረጋገጠ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ መከላከያ በተሠማራበት ሁሉ ከዕለት ጉርሱ እየቀነሰ ወገኑን እየደገፈ የሚገኝ ሠራዊት መሆኑን አመላክተዋል።

ባለፉት ዓመታት በርካታ ቤቶችን ከማደሱ ባለፈ የሚገባጠሙ ዘመናዊ ቤቶችን ገንብቶ ለአቅመ ደካማ ዜጎች አስረክቧል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም በችግር ውስጥ የነበሩ 16 አባዎራዎች ሲኖሩባቸው የነበሩ ደሳሳ ቤቶችን አፍርሶ ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ ቤቶችን በመገንባት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረጉን አስታውሰዋል።

መከላከያ ሠራዊት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የመኖሪያ ቤት የማደስ ተግባሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ የቤት ግንባታ ለተከናወነላቸው ዜጎች እንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሚኒስትሩ ደረጃውን የጠበቀ የሕንጻ ግንባታ ሥራ ላከናወነው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ምስጋና አቅርበዋል።

መከላከያ ደጀን ለሆነው ህዝብ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሩ አረጋግጠዋል። በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ የጠቅላላ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጄኔራል ታደሰ መኩሪያ በበኩላቸው፤ ለርክክብ የበቁት ቤቶች ፈጣን ቴክኖሎጂን በመጠቀም አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተጠናቀቁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ድጋፉ መከላከያ ሚኒስቴር የተመሠረተበትን 116ኛ ዓመት በሚከበርበት ወቅት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል ያሉት ሜጀር ጄኔራል ታደሰ ፤ ከቤት ግንባታ ባለፈ የተለያዩ ዜጎችን የሚደግፉ ሥራዎች ለወደፊቱም ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

መከላከያ ያስገነባቸው ሁለት ህንጻዎች 64 ቤቶችን የያዙ ሲሆን፤ ህንጻዎቹ ባለ አንድ መኝታ ቤቶችና 32 የንግድ ሱቆችን ያካተቱ ናቸው።

የቤት ዕድሉ ተጠቃሚ የሆኑና ከዚህ ቀደም ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አቅመ ደካሞችም መከላከያ ለሠላም ዘብ ከመቆም በዘለለ ለችግራቸው ስለደረሰላቸው ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በቤት ርክክብ ሥነ-ሥርዓቱ የመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖችና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ድጋፍ የተደረገላቸው ዜጎች ተገኝተዋል።

በሌላ ዜና የኢፌዴሪ አየር ኃይል ለስድስት ወር በመሠረታዊ ውትድርና ያሠለጠናቸውን ምልምል ወታደሮች አስመርቋል።

የኢፌዴሪ አየር ኃይል አዛዥ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ በተቋማዊ ሪፎርሙ ትኩረት ከተደረጉት መካከል የሰው ኃይል ግንባታ ዋነኛው ጉዳይ መሆኑንና በዚህም አየር ኃይሉ ዓለም ከደረሰበት የአቪዬሽን ቴክኖሎጂ ጋር እንዲራመድ በሚያስችል ጠንካራ አወቃቀር በመገንባት ለሀገሪቷም ኩራት የሆነ ተቋም መሆኑን ተናግረዋል።

## "ኢሬቻ ጥላቻን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት የእርቅና የይቅርታ በዓል ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ያለምንም የሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት በአንድነት የሚከበር ታላቅ የአደባባይ በዓል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ የአንድነት ተምሳሌት፣ የወንድማማችነት፣ የሰላምና የእርቅ እንዲሁም የኦሮሞ ሕዝብ ባህል ደምቆ የሚታይበት የሀገራችን የቱሪዝም መዳረሻነት የሚያጎለብት መሆኑን ጠቅሰው፤ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ አባገዳዎች ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት ዕሴቱን ጠብቆ በሰላም እንዲከበር የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ሲያከናውን እንደቆየ ተናግረዋል።

ኢሬቻ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የሚሳተፍበት በዓል እንደመሆኑ መጠን የኦሮሚያ፣ የአዲስ አበባና የፌዴራል የፀጥታ አካላት በዓሉ በሰላም እንዲከበር አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቀዋል ብለዋል።

በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ከፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት በዓሉ በሰላም እንዲከበር ለማስቻል ሕዝቡን ለማስተባበር እና ለመርዳት ዝግጅታቸውን መጨረሳቸውን ገልጸው፤ የአዲስ አበባ፣ ሸገርና የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች እንግዶቻቸውን ለመቀበል ዝግጅት ማድረጋቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ኢሬቻ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ የሚሳተፍበት ትልቅ ፌስቲቫል ነው። በመሆኑም የበዓሉ ታዳሚዎች በሰላም ወጥተው በሰላም ወደየቀዬያቸው እንዲመለሱ አባገዳዎች፣ ሀደ ሲንቄዎች፣ ቄሮና ቀሬ፣ የአዲስ አበባ፣ የሸገርና የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጠይቀዋል።

የየትኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ዓርማ ይዞ ወደ ኢሬቻ መምጣት ከበዓሉ እሴት ጋር የሚጻረር በመሆኑ እንደማይፈቀድ ገልጸው፤ የበዓሉ ተሳታፊዎች የአባገዳ ባንዲራን ብቻ በመያዝ አባገዳዎች ባስቀመጡት መሠረት በዓሉን እንዲታደሙ አሳስበዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ‹‹ኢሬቻ የአንድነትና የወንድማማችነት ዓርማ›› በሚል መሪ ቃል መስከረም 26 በአዲስ አበባ፣ መስከረም 27 ቀን 2016 ዓ.ም ደግሞ በቢሾፍቱ እንደሚከበር ተጠቁሟል።

## በአማራ ክልል በድርቅ ለተጎዱ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

እንደ አቶ አረጋ ገለጻ፣ ለችግር የተጋለጡ ወገኖች ፈጣን ድጋፍ እንዲያገኙ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የገባ ሲሆን፤ የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች በእጃችን ላይ ያለውን ሀብት በመጠቀም ድጋፍ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

በክልሉ የተከሰተው ድርቅ መጠነ ሰፊ ነው ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ ፤ በክልሉ ያለው ለድጋፍ የሚውል ሀብት ውስን ቢሆንም ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ዜጎችን ከችግር ለማውጣት ጥረት እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።

በዝናብ ዕጥረት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የዕህል ድጋፍ ለማድረግ የተወሰነው 430 ሚሊዮን ብር በቂ አለመሆኑን ጠቁመው፤ የክልሉ መንግሥት የችግሩን መጠን በመለየት ተጨማሪ አጋዥ ድርጅቶችን የማፈላለግ እና የማስተባበር ሥራ እንደሚያከናውን አመላክተዋል።

የተፈጠረው የዝናብ እጥረት አደጋ ከክልሉ ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር ተዳምሮ ተጨማሪ ጫና ቢሆንም መንግሥት ለተቸገሩ ዜጎች ለመድረስ ሁሉንም አይነት ጥረት እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

የዝናብ እጥረት ያላጋጠማቸው እና ትርፍ አምራች የሆኑ አካባቢዎች ለተቸገሩ ወገኖች ፈጥነው በመድረስ ወገናዊ አለኝታነታቸውን እንዲያረጋግጡም መልእክት አስተላልፈዋል።

የተከሰተው የሰላም እጦት የድጋፍ እህልና ቁሳቁስ ዝውውሩን ከማስተጓጎል በተጨማሪም የዝርፊያ ሙከራዎች መስተዋላቸውን አብራርተዋል።

"ለሁሉም ነገር መፍትሔ ለመስጠት መሠረቱ ሰላም ነው" ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን ሕይወት ለመታደግ ሃላፊነት የሚሰማው በሙሉ ለአካባቢው ሰላም ዘብ መቆም አለበት ብለዋል።

በዝናብ እጥረት፣ በመፈናቀል እና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡ ወገኖች ድጋፍ እንዲያገኙ እና በዘላቂነት እንዲቋቋሙ በቁርጠኝነት እንደሚሠራም ርዕሰ መስተዳድሩ አስገንዝበዋል።

## "ኢሬቻን ለማክበር ከውጭ ሀገር የሚመጡ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የባህል ዘርፍ ኃላፊ አቶ ብርሃኑ ቡጤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የዘንድሮው ኢሬቻ በዓል ባህል ወጉንና ሰላሙን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ቅድመ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፤ ከውጭ ሀገራት በዓሉን ለማክበር የሚመጡ እንግዶችንም በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለማስተናገድ ዝግጅት ተደርጓል።

እንደ አቶ ብርሃኑ ንግግር፤ በዓሉን በሚመለከት ከአባገዳዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የምክክር መድረክና ሌሎችም ዝግጅቶች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን፤ በዓሉን ኢትዮጵያ ጨዋነትን በተላበሰ መልኩ ለማክበር ታቅዷል።

በዓሉ ሰባ በሚሆኑ ስፍራዎች እንደሚከበር የተናገሩት አቶ ብርሃኑ፤ ከዚህ ቀደም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ ተሳታፊ እንደሚሆንበት በማውሳት ከነበሩት የበለጠ የሰው ብዛት ይታይበታል ተብሎ ይጠበቃልም ሲሉ ገልጸዋል።

ከሀገር ውስጥና ውጭ የሚመጡ አካላት በጥሪ የሚመጡና ባህሉን በማድነቅ በፍላጎት የሚመጡ መሆኑን የገለጹት አቶ ብርሃኑ፤ ከጎረቤት ሀገራት በተለይም ከኬንያ ከኡጋንዳና ብሩንዲ በዓሉን ለማክበር የሚመጣ የባህል ቡድን መኖሩን ተናግረዋል።

በዓሉ ሰላምን ፍቅርን አንድነትን ማዕከል ያደረገ መሆኑን በመቶ ሺህ ሳይሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ የሚያከብረው በመሆኑ በመግለፅ የቱሪዝም መዳረሻነቱን ማጉላት ስለማስፈለጉ ጠቅሰዋል።

ኢሬቻ ሁለንተናዊ ጥቅም እንዳለው የተናገሩት አቶ ብርሃኑ፤ ለሀገር አንድነት ገፅታ ግንባታ፣ ለማህበራዊ መስተጋብር ለኢኮኖሚ እድገት የቱሪዝም መዳረሻ በመሆኑ የገቢ እድገቱን የሚያጎለብት መሆኑንና የውጭ ሀገራት ቱሪስቶችንም ስለመሳቡም አብራርተዋል።

ከኦሮሞ ተወላጆች በተጨማሪ ከሀገሪቷ የትኛውም ጫፍ ላይ ያሉ ሁሉ የየራሳቸውን አልባሳት በመልበስና በባህላቸው በማጌጥ በአንድ አደባባይ የሚያሸበርቁበት በዓል መሆኑን የተናገሩት አቶ ብርሃኑ፤ በዓሉ የኦሮሞ ብቻ ነው ተብሎ በማይገመትበት ደረጃ ለማክበር ታቅዷል ብለዋል። ወንድማማችነትና ብሄራዊ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ ለማክበር ዝግጅት ስለመደረጉም አክለዋል።

በተለይ የአዲስ አበባው ኢሬቻ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትብብር እንደተዘጋጀ ያመላከቱት አቶ ብርሃኑ፤ የህዝቦችን አንድነትና ወንድማማችነትን ባጎላ ሁኔታ እንዲከበር ለማድረግ ሰፊ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

አቶ ብርሃኑ ኢሬቻ የተወሰነ አካላት የሚያከብሩትና የሚያስከብሩት ሳይሆን የሁሉም መሆኑን በመረዳት ሁሉም ህዝብ የድርሻውን ሊወጣ ይገባዋል በማለት መልእክት አስተላልፈዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል በመጪው ቅዳሜና እሁድ ማለትም መስከረም 26 ና 27 በአዲስ አበባና በቢሾፍቱ ከተማዎች ኢሬቻ የአንድነትና የወንድማማችነት አርማ በሚል መሪ ሃሳብ የሚከበር ይሆናል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# የጎዳና ተዳዳሪዎችን ሕይወት የማሻሻል ባለራዕይ

**ዳግም ከበደ**

በኢትዮጵያ ሰብዓዊነትና መደጋገፍ ባህል መሆኑን የሚያሳዩ እጅግ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል። የሀገሪቱ ሕዝብ የተቸገረንና አቅም በማጣቱ ድጋፍ የሚሻን ወገን በቡድንና በተናጠል በመሆን የሚደግፍባቸው የተለያዩ አደረጃጀቶች ባለቤት ነው። ከእነዚህ መንገዶች መካከል እቁብ፣ እድር እና የመሳሰሉት ዘመናትን ያስቆጠሩ እሴቶቹ ይጠቀሳሉ። "ወገን ለወገኑ ደራሽ ነው" የሚል የቆየ ብሂልና በጎ ልምድ ያለው ኢትዮጵያዊ የጎረቤቱን እና የአካባቢውን ልጅ እንደራሱ ልጅ ቆጥሮ የማሳደግና የማስተማር ባህል አለው።

ዛሬ ይህንን እሴት የሚጋራ አንድ ሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት ስለሚሰራው ምግባር ሰናይ ተግባር ጥቂት ዳሰሳ ለማድረግ ወድደናል። ይህ ሀገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት በኢትዮጵያዊ የበጎነት ስሜትና የመተጋገዝ መንፈስ ላለፉት 22 ዓመታት ጎዳና ለመውጣት የተገደዱ ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን ጨምሮ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ውስጥ የወደቁ የማህበረሰብ ክፍሎችን እየደገፈ፣ በሁለት እግራቸው እንዲቆሙ ምክንያት እየሆነ ይገኛል።

ድርጅቱ ‹‹ኒው ላይፍ›› ይባላል። የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሄለን ጥላሁን ‹‹ድርጅታችን ጎዳናዎች የሰዎች መኖሪያ ሳይሆኑ መረማመጃዎች ናቸው ብሎ ያምናል።›› ትላለች፡፡ ሥራ አስኪያጇ ለሰው ልጅ ክብር እንደሚገባም ጠቅሳ፣ ‹‹ማንም ሰው ጎዳና ላይ መኖር የለበትም ብለን ራዕይ ይዘን ነው ድርጅቱን ለመመስረት የተነሳ ነው›› በማለት ትገልጻለች። ድርጅቱ ሴቶች ሕፃናትና ወጣቶችን አምራች ዜጋ ለማድረግ ዋና ግብ አስቀምጦ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት መመስረቱን ታስታውሳለች።

በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ ጎዳና ላይ በሚኖሩ ሕፃናት፣ ሴቶችና እናቶች ተጨናንቋል የምትለው ሥራ አስኪያጇ፣ ይህ አሃዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱንም ትናገራለች። በተለይ ኒው ላይፍ በተመሰረተበት ወቅት የነበረው ጎዳና ላይ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር አሁን ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ማሻቀቡን ጠቅሳለች።

የማህበረሰቡ ክፍል የሆኑት እነዚህ ዜጎች ጎዳና እንዲወጡ ከሚገደዱባቸው ዋንኛ ምክንያቶች ውስጥ የኑሮ ውድነት፣ ጦርነት፣ የቤተሰብ ልጆችን በኃላፊነት የማሳደግ አቅም ማጣት፣ የተሻለ ሕይወት ይኖራል የሚል የተሳሳተ ግምትና የግንዛቤ እጥረት እንደሚጠቀሱ ትገልፃለች። በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ሴቶችና ሕፃናትን ሳይጨመር ከ100 ሺህ በላይ ሕፃናት መኖራቸውን መረጃዎችን ዋቢ አርጋ የምትጠቅሰው ወይዘሮ ሄለን፣ ይህም የጎዳና ሕይወት ምን ያህል አስከፊ ደረጃ እየደረሰ መሆኑን ያሳያል ትላለች።

‹‹ዜጎችን ከጎዳና የማንሳት ሥራ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባና ክቡር የሰው ልጅ ሕይወትን ገፅታ በእጅጉ የሚያበላሽ ነው›› ስትል ገልጻ፣ ለበርካታ ዓመታት በጎዳና ላይ የሚገኙ ሕፃናትን፣ ወጣቶችን በማንሳትና ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ በመሥራት የሚታወቀው ድርጅቱ፣ ዋናው ትኩረቱን ይህን ማድረግ የፈለገበትን ምክንያት ትገልፃለች።

ሥራ አስኪያጇ እንዳለችው፤ ‹‹ኒው ላይፍ›› ጎዳና የወጡ የማህበረሰቡ አካል የሆኑ ሕፃናትና ወጣቶችን ለማቋቋም አልሞ የተመሰረተው በሁለት ባለትዳሮች ነው። እነሱም ሰላማዊት ቡቻና ብርሃኑ ጣሰው ይባላሉ። በወቅቱም ድርጅቱ በጎዳና ላይ ያሉ ልጆችን በመሰብሰብ የምግብ፣ የንፅህና እና የሥነ ምግባር ትምህርትን ጨምሮ በርካታ ድጋፎች ያደርግ ነበር። በተጨማሪ ድርጅቱ የተለያዩ የእጅ ሥራ ሙያዎችን በማስተማር ራሳቸውን እንዲችሉ እድል ይፈጠር ነበር።

በጊዜው ‹‹ኒው ላይፍ›› ባደረገው ድጋፍ ምክንያት አሁን ላይ ከጎዳና ተነስተው ኢንጂነር፣ ዶክተር፣ መምህር፣ በተለያዩ የሥራ መስኮች እስከ ማናጀርነት የሥራ መስክ የደረሱ እንዲሁም የራሳቸውን የግል ሥራ መስርተው ውጤታማ የሆኑ በርካታ ውጤታማ ሰዎች መፈጠራቸውን የምትገልጸው ወይዘሮ ሄለን፤ አሁንም ድረስ ይህንን በጎ ምግባሩን አጠናክሮ መቀጠሉንና በጎዳና ሕይወት ውስጥ ያሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎችን የሚታደግ ሥራ እንደሚሰራም ትናገራለች።

"የሚውሉበትንና የሚያድሩበትን አካባቢ መሠረት አድርጎ ማህበረሰቡ የሚሰጣቸው አመለካከት፣ የሚፈጥርባቸው ተፅእኖ እንጂ፣ በመርህ ደረጃ በጎዳና የሚኖሩ ዜጎች በቀዳሚነት ፍቅርን ይፈልጋሉ" የምትለው የኒው ላይፍ ሥራ አስኪያጇ ወይዘሮ ሄለን፤ በተገቢው መንገድ ማህበረሰቡ ቢያቀርባቸውና ቢደግፋቸው እንደማንኛውም ዜጋ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ መሆናቸውን ትገልፃለች። ከዚህ መነሻ ድርጅታቸው እነዚህን ዜጎች በሚኖሩበት ቦታ በመሄድ እንደ እህትና ወንድም ፍቅር በመስጠት እና ችግራቸውን ቀርቦ በመረዳት ድጋፍ ለማድረግ እንደሚጥር ትናገራለች።

እንደ ሥራ አስኪያጇ ገለፃ፤ ‹‹ኒው ላይፍ›› በጎዳና ላይ የሚኖሩ ዜጎችን በተከታታይ በማግኘት ፍቃደኛ እስኪሆኑ ድረስ አቅርቦ በማነጋገር የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ያደርጋል። ከዚህ በመቀጠልም ወደሚያዘጋጀው ማዕከላት በማስገባት የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ ስልጠናዎችን በባለሙያዎች ይሰጣል። በተለይ እነርሱ በማህበረሰቡ፤ ማህበረሰቡ በእነርሱ ላይ ያላቸውን አሉታዊ አመለካከት የሚያሻሽሉ ግንኙነቶችና ሥልጠናዎችንም በመስጠት ግንኙነቶችን ለማሻሻል ይሰራል።

ሥራ አስኪያጇ እንዳብራራችው፤ በመጀመሪያው ሶስት ሳምንት ወደ ማዕከሉ የሚገቡ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ዜጎች የሚረጋጉበት እና የለመዱትን ያልተገባ ባህሪ /'ሱስ'/ እንዲቀንሱ የሚደረግበት ነው"፡፡ ይህንን እርከን ሲያልፉ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት የሕይወት ክህሎት እንዲያገኙ በማስቻል ቤተሰብ ያላቸውን ወደ ቤተሰባቸው መመለስ፣ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የተጠፋፉትን በማገናኘት፣ ቤተሰብ የሌላቸውን ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በማገናኘት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ልዩ ልዩ ሥራዎችን ያከናውናል።

የማህበረሰቡ አካል የሆኑት በጎዳና ላይ የሚኖሩ ዜጎች አስቀድመው ወደዚህ ሕይወት ውስጥ እንዳይገቡ የመከላከል ሥራ ካልተሰራ የችግሩን ምንጭ ማድረቅ አይቻልም፡፡ በዋናነት ይህንን ችግር ለመቅረፍ መሥራት ያለበት በማህበረሰቡ ውስጥ መሆኑን ኒው ላይፍ አምኖ፣ አዲስ ስትራቴጂክ እቅድ ነድፎ እየሰራ ነው። በእቅዱ መሠረትም በቀዳሚነት ዜጎች ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት የመከላከል ሥራ ላይ አተኩሮ እየሰራ ይገኛል።

"ልጆቿን ብቻዋን የምታሳድግ እናት እዚያው ማህበረሰቡ ውስጥ እያለች ወደ ጎዳና ሳትወጣ ልንደርስላት ይገባል" የምትለው የኒው ላይፍ ሥራ አስኪያጅ፤ እነዚህን መሰል እናቶች ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ፣ በኢኮኖሚ የገቢ ምንጭ እንዲያገኙና የማህበረሰቡ ጠንካራ አካል እንዲሆኑ መሥራት ከምንም ነገር በላይ ወደ ጎዳና የሚወጡ ዜጎችን ቁጥር እንደሚቀንሰው ትናገራለች።

ሥራ አስኪያጇ እንዳለችው፤ ‹‹ኒው ላይፍ›› በቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠሩ ግጭቶችና የሰላም እጦት ከልዩ ልዩ አካባቢዎች የተፈናቀሉ ዜጎችን የመደገፍ ሥራም ይሰራል፡፡ በተለይ ከፕላን ኢንተርናሽናል ጋር በመተባበር 21ሺ አካባቢ ከሚደርሱ በደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኙ ስደተኞችን መካከል እርሱ መደገፍ የሚችለውን ያህል በመለየት (አካል ጉዳተኛ ሴቶች፣ እናቶች እና አቅመ ደካሞችን፣ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶችን) እየረዳ ነው። እነዚህን ዜጎች አቅማቸው በፈቀደው መጠን መደገፍ መቻሉ ነገ ደጋፊ አጥተው ጎዳና እንዳይወጡና እንዳይበተኑ ማድረግ ያስችላል፡፡ ይህን መሰሉ ተግባርም የድርጅቱ የቅድመ መከላከል ተግባሩ ነው፡፡

"ኒው ላይፍ 30 ሺህ የሚደርሱ ዜጎች ላይ በጎ ተፅእኖ መፍጠር ችሏል" የምትለው ሥራ አስኪያጇ፤ ከጎዳና አንስተው ዩኒቨርሲቲ ለመግባት አንድ ዓመት ከቀራት ተረጂ አንስቶ በርካታ ችግሮችን ውጣ ውረዶችን እንዲያልፉ ድጋፍ እስካደረጉላቸው በርካታ ሺህ ወጣቶች ድረስ በጎ ተፅእኖ መፍጠር መቻሉን ትናገራለች። "ኢትዮጵያውያን የት ቦታ መርዳት እንዳለባቸው ላይገነዘቡ ይችላሉ፤ እንጂ ንፉግ አይደሉም" በማለትም እነዚህን ወገኖች ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራታቸው እንዲያገግሙ ለማድረግ እጃቸውን በቀናነት የሚዘረጉና ድርጅታቸውን የሚደግፉ ብዙሃን እንዳሉም ትገልፃለች።

ድርጅቱ ‹‹ኒው ላይፍ›› በርካታ እናቶች በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ፣ ተደማጭነታቸው እንዲጨምር ማድረጉን የምትገልፀው ወይዘሮ ሄለን፤ አንድ እናት በኢኮኖሚ አቅሟ የጎለበተች ስትሆን የውሳኔ ሰጪነትና ቤተሰብን የመምራት ኃላፊነት የመውሰድ አቅም እንደምትፈጥር ትናገራለች። በዚህ ምክንያት ‹‹ኒው ላይፍ›› መሰል አቅም እናቶች እንዲኖራቸው እቅድ ነድፎ



ወይዘሮ ሄለን ጥላሁን

**ድርጅቱን በድጋፍ የሚቆም ሳይሆን ራሱን የቻለና ለኢትዮጵያውያን ምርኩዝ መሆን የሚችል ግዙፍ ተቋም ለማድረግ ታልሞ እየተሠራ ነው**

መሥራቱንና አሁንም ድረስ በዚህ ተግባሩ መቀጠሉን ትገልፃለች።

"ኢትዮጵያ ከናይጄሪያ ቀጥሎ ከአፍሪካ በርካታ ወጣቶች የሚገኙባት ሀገር ነች" የምትለው ሥራ አስኪያጇ፣ ይህንን አቅም በሥራ ፈጠራ፣ በልማት እና ለሀገር በሚጠቅም አቅም በሚፈለገው ልክ እየተጠቀምንበት እንዳልሆነ ትናገራለች። ይህንን ችግር ለመቅረፍም ድርጅታቸው እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ወጣቶችን በተለያየ መልኩ በማብቃት ተግባር ላይ እየተሳተፈ መሆኑንም ትገልፃለች።

እሷ እንዳለችው፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥም በአዲስ አበባ "በአዲስ ከተማና አራዳ ክፍለ ከተሞች" አራት ሺህ የሚደርሱ ወጣቶችን "በሥነ ምግባር የታነፁ፣ ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገር የሚሆኑ ወጣቶች እንዲሆኑ" የሚያስችል ሥልጠናና የማብቃት ሥራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ ባሻገር 100 እናቶችን ከፕላን ኢንተርናሽናል ጋር በመሆን የራሳቸውን የንግድ ሃሳብ አውጥተው ሥራ እንዲጀምሩ አስችሏል። በቅርቡም በሰላም ላይ በመሥራት በሲቪል ሶሳይቲ ዘርፍ እየተሳተፈ ይገኛል።

‹‹ኒው ላይፍ›› የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ነድፎ እየሠራ መሆኑን የምታነሳው ሥራ አስኪያጇ፤ ድርጅቱ በድጋፍ የሚቆም ሳይሆን ራሱን የቻለና ለኢትዮጵያውያን ምርኩዝ መሆን የሚችል ግዙፍ ተቋም እንዲሆን ታልሞ እየተሰራ መሆኑንም ትገልፃለች። ከዚህ መነሻ በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱን በራሱ የፋይናንስ አቅም እንዲፈጥርና ፕሮጀክቶችን እንዲተገብር የሚያስችል እንዲሆን እንደሚሰራ ትናገራለች።

በሁለተኛነት ትውልዱ በሥነ ምግባር፣ በእውቀት እና ክህሎት የተሻለ ሆኖ እንዲወጣ የሚያስችል ማዕከል የመገንባት ህልም እንዳለም ትገልፃለች። ይህ ሁሉ የሚሳካው ግን መንግሥት፣ ማህበረሰቡ እና እያንዳንዱ ዜጋ "ኒው ላይፍን" ልክ እንደራሱ አድርጎ ማገዝና መደገፍ፣ ለአላማው መሳካትም አብሮ መቆም ሲችል እንደሆነ ታመለክታለች። ለዚህም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ድጋፍና እገዛ ጠይቃለች። ከዚህ መነሻ ‹‹ኒው ላይፍ›› በአሥር ዓመት ውስጥ የልህቀት ማዕከልና ለወገኑ የሚደርስ ትልቅ ማዕከል እንደሚሆን ሥራ አስኪያጇ ሄለን ቃል ገብታለች።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## እሬቻ፤ ዕርቅና ሰላም

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ በርካታ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት የሚከበሩባት ሀገር ናት። በክርስትና እምነት ከሀገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና የተሰጣቸው የጥምቀትና የመስቀል ደመራ በዓላትን መጥቀስ ይቻላል። በእስልምና እምነትም እንዲሁ ከዚህ ባሻገር በሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የሚከበሩ እንደ ሲዳማ ፊቼ ጨምበላላ አይነት ታላላቅ በዓላት አሏት፡፡ እነዚህ የማይዳሰሱ በዓላት የቱሪስት መስህብ በመሆን ለሀገሪቱ የሚያበረክቱት የኢኮኖሚ ፋይዳ ትልቅ ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ከእነዚህ በዓላት መካከል በዩኔስኮ የተመዘገበው የገዳ ሥርዓት አካል የሆነውና በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ በትልቅ ደረጃ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል አንዱ ነው።

የኢሬቻ በዓል በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ከሚከበሩ በዓላት ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዝ ክብረ በዓል ነው። በዓሉ የሚከበረው የክረምት ወቅት አልቆ የፀደይ ወቅት በሚጀምርበት ወቅት ነው። የዝናብ፣ የጎርፍ እና የጨለማን ወቅት አሻግሮ ለፀደዩ ብርሃን ላዳረሰ አምላክ ምስጋና በማቅረብ ማለት ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢሬቻ በዓል በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ አህጉር በቀል ሆኖ በብዙ ሚሊዮኖች የሚከበር እና በሚሳተፈው የሕዝብ ቁጥር ተወዳዳሪ የሌለው በዓል ነው። ይህ ማለት የኢሬቻ በዓል የኦሮሞም ብቻ ሣይሆን በምስራቅ አፍሪካ ጭምር ታላቅ በዓል እየሆነ ስለመምጣቱ ማሳያ ነው።

የኢሬቻ አጀማመር በገዳ አቆጣጠር (አንድ ገዳ 7 ዓመት ከ8 ወር ወይም 8 ዓመት) ከ6 ሺህ 660 ዓመት በፊት የተጀመረ እንደሆነ አዋቂዎች ይናገራሉ። የገዳ ሥርዓት ባለበት፤ የኦሮሞ ሕዝብ በሚገኝበት ሁሉ ኢሬቻ አለ። በዓሉ ዋቄፈንና ከተባለውና ከጥንቱ የኦሮሞ ሕዝብ እምነት የፈለቀ እንደሆነም ይጠቀሳል።

የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የኢሬቻ በዓልን ያከብራል ይላሉ የማኅበረሰብ ባህላዊ መሪዎች። ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱ በማለፉ በኢሬቻ ቀን ምስጋናውን ለፈጣሪ ያቀርባል። በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ መስከረም ላይ ይገናኛል። ሕዝቡም ክረምቱን በፈጣሪ ፍቃድ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከዘመድ አዝማድ አገናኘን ብሎ ምስጋናውን ለፈጣሪ ያቀርባል።

የኦሮሞ ሕዝብ የኢሬቻ በዓልን ለማክበር ሲወጣ እንደ ሣር ወይም አበባ ያሉ እርጥብ ነገሮችን በእጁ ይዞ ይወጣል። የዚህ ትርጉምም ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው፤ ለዚህም እናመስግንሃለን በማለት እርጥብ ነገር ተይዞ ይወጣል፡፡ ሲሉ የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ።

በበዓሉ ተሳትፎ ሰፊ ድርሻ ካላቸው አካላት መካከል ወጣቶች በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናቸው፤ ወጣት ጀን አሕመድ ከበዓሉ ተሳታፊና አስተባባሪ ከሆኑ ወጣቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ እርሱ እንደሚናገረው፤ የኦሮሞ ሕዝብ ገዳ የሚባል የሃይማኖት፣ የአስተዳደር የዕርቅና መሰል እሴቶችን ይዞ የኖረ ሕዝብ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የኢሬቻ በዓል የኦሮሞ ሕዝብ ጌታውን የሚያመሰግንበት ሥርዓት ነው ይላል።

የኢሬቻ በዓል በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚከበር የሚገልፀው ወጣት ጀን የመጀመሪያ ኢሬቻ ቱሉ የሚል ስያሜ ያለውና በተራራ ላይ የሚከበር ሲሆን ሌላኛው በወንዝ ዳር የሚከበረው ኢሬቻ መልካ እንደሆነ ያስረዳል። በተራራ ላይ የሚደረገው ኢሬቻ በጋውን በሰላም አሳልፈናል ክረምቱ ደግሞ የሰላም ይሁንልን ተብሎ ለፈጣሪ አደራ የሚሰጥበት ኩነት ነው ይላል፡፡

ላለፉት ዓመታት በዓሉ ተዳክሞ ስለመቆየቱ የሚናገረው ወጣት ጀን ሕዝቡ በተለይም ወጣቱ ባደረገው ትግል ይህንን በዓል መመለስ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ወጣቱ ዕሴቱን በጠበቀ፤ ሰላማዊ በሆነ፤ ውበት ባለው መልኩ ህብረ ብሔራዊ አንድነትን በጠበቀ መልኩ መከበር እንዳለበት ይናገራል።

በዓሉ ሰላማዊ ሆኖ እንዲከበር ወጣቶች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው የሚገልጸው ጀን በበዓሉ በቅድሚያ ሴቶች፤ በመቀጠል አባ ገዳዎች፤ በሶስተኛ ደረጃ ወጣቶች



ወጣት ከድር እንዳልካቸው



ወጣት ጀን አሕመድ

ሆነው ወደ ወንዝ "መሬሆ" እያሉ ሲወርዱ ወጣቶች ወይም ቄሮዎች ኃላፊነታቸው በዓሉ ያለ አንዳች ኮሽታ ከየትኛውም ፖለቲካዊና መሰል ጉዳይ ነፃ ሆኖ እንዲከበር ማስቻል ነው፡፡ ኢሬቻ የሕዝብ በዓል እንደመሆኑ እሴቱን ጠብቆ ፈጣሪውን ብቻ በሚያመሰግንበት መንገድ ተከብሮ እንዲያልፍ ወጣቶች መወጣት ያለባቸው ሚና ትልቅ እንደሆነ ገልጿል።

በዓሉ ሰላማዊ ሆኖ እንዲከበር በአዲስ አበባ፣ በሸገር ከተማና በቢሾፍቱ የሶስቱም ከተማ ወጣቶች አንድ ላይ በመሆን እየሰሩ እንደሆነ የሚናገረው ወጣት ጀን በኢሬቻ በዓል አገልግሎት ላይ የሚውሉ ማንኛቸውም ነገሮች ባህልና እሴቱን ጠብቀው እንዲከበሩ በወጣቶች የሚዜሙ የባህል ጨዋታዎች ሳይቀር ተሰንደው ዝግጅት ተደርጎ የባህል ቡድን ተቋቁሞ እየተሰራ እንደሆነ ገልጿል።

ከተለያዩ ሀገራት ማለትም ከኬንያ፣ ከታንዛኒያ፣ ከሶማሊያ ከአውሮፓ ጭምር የበዓሉ ታዳሚ ለመሆን የሚመጡ እንግዶች የበዓሉን ምንነትና ታሪክና እሴት እንዲያውቁ የማስተዋወቅ ሥራ ለመሥራት ወጣቶች የኢሬቻ አምባሳደር ሆነው ኃላፊነት ለመወጣት ተዘጋጅተዋል ያለው ጀን፤ በተሳታፊዎች የሚያዙ ጽሑፎች ኢሬቻን ብቻ የሚገልፁ እንዲሆኑ፣ የሚያዝ ባንዲራ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እውቅና ያለው ባንዲራና የአበገዳ ባንዲራ እንዲሆን በዚህ አግባብ ወጣቶች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዝግጁ እንደሆኑ ተናግሯል።

በሸገር ከተማ አስተዳደር ስር የሚከበሩ ሁለት የኢሬቻ በዓላት እንዳሉ የሚናገረው ወጣት ጀን እነዚህም በሰበታና ቡራዩ የሚከበሩ እንደሆኑ ተናግሯል፡፡ ይህ ማለት በአዲስ አበባና ቢሾፍቱ ከሚከበሩ በዓላት ጋር አንድ ላይ ትልቅ ኩነት ሆነው የሚያልፉ እንደሆኑና እነዚህ ሁሉ በሰላም ተከብረው እንዲያልፉ በየደረጃው ያለው ወጣት በየአካባቢው ተደራጅቶ ተወያይቶ የበዓሉን ዕለት እየጠበቀ እንደሆነ ገልጿል።

ኢሬቻ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ባህል እየሆነ መጥቷል የሚለው ወጣቱ፤ የዓለም ጥቁር ሕዝብ የራሱ የሆኑ እሴቶች ሃይማኖቶች፣ መተዳደሪያ ሕጎች እንዳሉትና ኢሬቻ ከዚህ አንፃር ትርጉሙ ከፍ ያለ መሆኑን ያስረዳል። ‹‹ማንኛውም ሰው ኢሬቻ ለማክበር ከመሄዱ በፊት ለአምላኩ ምስጋና ከመቅረቡ በፊት ሰው ሁሉ መታረቅ አለበት›› ይላል፡፡ እርስ በእርሱ ሰላም አውርዶ ሆዱ ንፁህ ሆኖ ከቂምና በቀል ወጥቶ ነው ኢሬቻን ማክበር የሚችለው የሚለው ወጣት ጀን፤ ይህ እንደ ሀገር ሰላምን ለማውረድ ዕርቅን ለማስተማር ትልቅ ዋጋ ያለው በዓል ነው ይላል።

ጀን እንደሚያብራራው ይህንን በዓል ደግሞ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አውቀው የእርሳቸው አድርገው ተቀብለው ማክበር አለባቸው፡፡ በዓሉ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የባህልና የሳይንስ ተቋም(UNESCO) ተመዝግቦ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ማግኘት እንዲችል መሥራት እንዳለባቸው ተነግሯል።

ከዚህ ውጭ የኢሬቻን ትላልቅ ዕሴቶች ለዓለም ማስተዋወቅ እንዳለ ሆኖ በበዓሉ ላይ የተደረጉ የስም መጥፋት ሥራዎች ትክክለኛውን የኢሬቻ ምንነት በማጉላት ማስተካከል ያስፈልጋል የሚለው ወጣት ጀን በዓሉ ያለው አንድምታ መልካም ብቻ እንደሆነ ሁሉም ግንዛቤ እንዲኖረው መሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራል።

**የኦሮሞ ሕዝብ የኢሬቻ በዓልን ለማክበር ሲወጣ እንደ ሣር ወይም አበባ ያሉ እርጥብ ነገሮችን በእጁ ይዞ ይወጣል። የዚህ ትርጉምም ፈጣሪያችን ሆይ አንተ ያጸደቅከው ነው አብቦ ፍሬ ያፈራው፤ ለዚህም እናመሰግንሃለን በማለት እርጥብ ነገር ተይዞ ይወጣል**

በሚሊዮን የሚቆጠር ሰው በዓሉን ለማክበር ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ባዶ እጁን ሳይሆን በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይዞ ነው የሚመጣው የሚለው ወጣት ጀን ይህንን ገንዘብ አዲስ አበባ ላይ ለግብይት የሚያውለው ስለሆነ ሁሉም ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ተጠቃሚ ለመሆን መጣር እንደሚገባው ያስረዳል። ይህ ደግሞ ለከተማዋ ተጨማሪ የኢኮኖሚ አቅም እንደሚፈጥር ይናገራል፡፡

ስለዚህ የአዲስ አበባ ሕዝብ ኢሬቻን ብቻ ሳይሆን ሌሎች በዓላትም በከተማዋ እንዲከበሩ ተባባሪ መሆን እንዳለበትም ይናገራል፡፡ በተለያዩ የዓለም ሀገራት በሚደረጉ ፌስቲቫሎች የሚገኘው ገቢ ትልቅ መሆኑንና ኢሬቻም በዚህ ረገድ ትልቅ ፋይዳ ስላለው የአዲስ አበባ ሕዝብ የበዓሉን ታዳሚ በፍቅር በማስተናገድ ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ባለፈ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ከፍ በሚያደርግ መልኩ በዓሉን ለማክበር መዘጋጀት እንዳለበት ተናግሯል።

ኢሬቻ ሁሉን አቀፍነቱን፣ ዲሞክራሲያዊናቱን፣ አብሮ መኖርን እና ይቅርታን ያቀፈ በዓል ነው የሚለው ወጣት ጀን እነዚህን እሴቶች ይበልጥ በማስተዋወቅ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የእራሱ በዓል መሆኑን አውቆ ተሳታፊ እንዲሆን እና በሁሉም ረገድ በተለይ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው ወጣት ጀን መልዕክቱን አስተላልፏል።

ወጣት ከድር እንዳልካቸው የኦሮሚያ ወጣቶች ማህበር ፕሬዚዳንትና የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ ነው። እርሱ እንደሚናገረው ኢሬቻ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በዓል ሲሆን የሰላም ምልክት ተደርጎም ይወሰዳል ይላል። ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ሰማይና ምድርን ለፈጣሪው ምስጋና የሚያደርስበት በዓል ነው። ከዘመን ወደ ዘመን ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና ያቀርባል፤ የሚመጣውን ዘመንም አምላክ የብራ አድርግልን ብሎ ፀሎቱን ለፈጣሪ ያቀርባል ይላል።

ወጣት ከድር እንደሚናገረው፤ በዚህ በዓል የወጣቶች ኃላፊነት ትልቅ ነው፡፡ በዓሉ የሕዝብ ሆኖ ሳለ ከዚህ ባፈነገጠ መልኩ ችግርና ሁከት ለመፍጠር የተዘጋጁ አካላት ስለሚኖሩ ይህንን አውቀው አካባቢያቸውን በንቃት መጠበቅ እንዳለባቸው እንደ ኦሮሚያ ከአራት ሚሊየን በላይ ወጣቶችን በዚህ ጉዳይ ላይ በማወያየት በዓሉ ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከበር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እንደተሰሩ ተናግሯል።

ከአዲስ አበባ አንድ ሺህ ወጣት፣ ከሸገር ከተማ አንድ ሺህ ወጣት በመመልመል ውይይት መደረጉንና በአዲስ አበባ ደረጃ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ከፀጥታ ስጋት ነፃ ሆኖ እንዲከበር ዝግጅት መደረጉን ጠቁሟል፡፡ በቢሾፍቱም እንዲሁ ወጣቶች ተደራጅተው አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ በማድረግ ክብረ በዓሉ ሰላማዊ ሆኖ እንዲከበር ዝግጅት ተደርጎ መጠናቀቁን ተግሯል።

በአዲስ አበባ ዙሪያ በሸገር ከተማ አስተዳደር ከ50 ሺህ በላይ ወጣቶች "በፎሌ" በመደራጀት ሰለምን ለማስጠበቅ ሥራዎች እንደተሰሩ የሚናገረው ከድር፤ ከየአካባቢው ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ወጣቶች ደግሞ በዓሉ በሰላማዊ መልኩ እንዲከበር የየድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው የጋራ መግባባት መፈጠሩንም ጠቁሟል፡፡ በዓሉ የኦሮሞ ሕዝብ የምስጋና በዓል እንጂ የየትኛውም ቡድን የፖለቲካ ትርፍ ማግኛ መድረክ እንዳልሆነ ተገንዝቦ ሁሉም የበዓሉ ታዳሚ ወጣት የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ተደርጓል ብሏል።

ኢሬቻ በአዲስ አበባ ብቻ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተገኝተው የሚያከብሩት በዓል ነው የሚለው ወጣት ከድር፤ ይህ ትልቅ ፌስቲቫል በምንም ሁኔታ በሚፈጠሩ አሉታዊ ነገሮች መጠልሸት እንደሌለበትና ለከተማዋ ተጨማሪ ጥቅምና ውበት ሆኖ ተከብሮ እንዲያልፍ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ በበዓሉ ሰርጎ በመግባት ሁከትና ግርግር በመፍጠር በዓሉን ለማደፍረስ የሚንቀሳቀስ አካል ካለ ደግሞ በንቃት በመጠበቅ ለኢሬቻ በዓል ድምቀት የሚጠበቅበትን ለመወጣት ሁሉም ዝግጁ መሆን እንደሚጠበቅበት አስረድቷል፡፡

በዓሉ የሚከበረው አባ ገዳዎች ባስቀመጡት አቅጣጫ መሠረት ነው የሚለው ወጣት ከድር ይህ ማለት በዓሉ ላይ ይዞ መገኘት የተፈቀደውንና የተከለከለውን ነገር በደንብ በመገንዘብ አባ ገዳዎችን ትዕዛዝ ማክበር እንደሚያስፈልግ ተናግሯል፡፡ ወደ በዓሉ ማንኛውም ሰው ሲመጣ ኢሬቻን ለማክበር እንጂ ሌላ ዓላማ ይዞ መምጣት የለበትም ብሏል።

የኦሮሞ ባህል መከባበርን አንድነትን ፍትህን ነው የሚያስተምረው የሚለው ወጣት ከድር፤ በበዓሉ የሚገኙ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን በሚያጠናክር መልኩ በአንድነት ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ኢሬቻ ሰላም ዕርቅና ፍቅርን የሚሰብክ ነው፡፡ ይህንኑ እሴቱን በጠበቀ መልኩ ለማክበር መዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ ገልጿል።

ወጣቶቹ ባስተላለፉት መልዕክት የኦሮሞ ሕዝብ ቱባ ባህል ከሚገለጽባቸው ሁነቶች አንዱ የሆነው የኢሬቻ በዓል ዓለም አቀፍ ተቀባይነቱን ከፍ ማድረግ በሚቻልበት መልኩ እንዲከበር ወጣቶች ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ የተለመደ እንግዳ ተቀባይነቱን በማሳየት በዓሉን በደመቀ መልኩ ለማክበር መዘጋጀት እንደሚገባ ወጣቶቹ ተናግረዋል፡፡

# የምድር በረከት

# ተስፋ የተጣለበት የድንጋይ ከሰል ማዕድን ልማት

ወርቅነሽ ደምሰው

“የድንጋይ ከሰል” የኃይል ምንጭ አማራጭ በመሆን በኢንዱስትሪዎች ውስጥ በእጅጉ ከሚፈለጉ ማዕድናት መካከል አንዱ ነው፡፡ ከኢንዱስትሪዎቹ ቀደም ሲልም የሰው ልጅ ከሚጠቀምባቸው ጥንታዊ የኃይል አማራጮች አንዱም ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜም ይህ ማዕድን የተለያየ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች በኃይል አማራጭነት በእጅጉ ይፈልጉታል።

የድንጋይ ከሰል ከኢንዱስትሪ ልማት ጀምሮ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የኃይል ምንጭ ሆኖ ማገልገሉ ተፈላጊነቱ የበለጠ እየጨመረ እንዲመጣ አስችሎታል፡፡ ቤቶችን ለማሞቅ፣ በኢንዱስትሪ ውስጥ ምድጃዎችን ለማሞቅ እና ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የሚያገለግል ሲሆን፣ ማዕድኑን አልምቶ ለውጭ ገበያ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማግኘትም ይቻላል፡፡

በማዕድኑ ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎችን ዋቢ ያደረጉ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያላቸው ብዙ ዓይነት ንጥረ ነገሮች ከድንጋይ ከሰል ማግኘትም ይቻላል፡፡ ሰልፈር፣ ቫናዲየም፣ ዚንክ እና መሰል ማዕድናትን የያዘ ማዕድን መሆኑ ይገለጻል፡፡

በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች የድንጋይ ከሰል ዘላቂና አስተማማኝ የኃይል ምንጭ መሆኑን ይገልፃሉ። ባለሙያዎቹ በተፈጥሮ ይዘቱ ኃይል የማውጣት አቅሙ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት እንደሚረዳና ተመራጭ እንደሚያደርገው ያመለክታሉ። የድንጋይ ከሰል እንደ ጋዝ ወይም ፈሳሽ ወደ ተለያዩ ቅርጾች ሊቀየር ይችላል። ይህም የድንጋይ ከሰሉ የበለጠ ንፁህ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማቃጠል እንዲችል እንደሚረዳ ነው እነዚሁ ባለሙያዎች የሚናገሩት። የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ እንደ ባዮማስ ካሉ ታዳሽ የኃይል ምንጮች ጋር መጠቀም የሚያስችል አማራጭ እንደሚሰጥም የዘርፉ ተመራማሪዎች ያብራራሉ።

በዓለም ላይ የተለያዩ የድንጋይ ከሰል አይነቶች ቢኖሩም፣ ሁሉም በሚባል ደረጃ አስፈላጊ ግፊትና የሙቀት መጠን መነሻ አላቸው፤ የጥራት ደረጃቸው ግን በተለያዩ ምክንያቶች ከፍ ወይም ዝቅ ያለ ሊል ይችላል። ሁሉም የድንጋይ ከሰል ከፍተኛ የሙቀት አቅም ያለው ኃይል ማመንጨት የሚችሉ በመሆናቸው፣ ይህም ሁኔታ የድንጋይ ከሰል በዓለም ላይ አንዱ ኃይል ማመንጫ እንዲሆን እንዳስቻሉት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በርካታ የድንጋይ ከሰል ዓይነቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ከእነዚህም መካከል የካርቦን ይዘታቸው ከፍተኛ የሆነ በተለየ መልኩ ከፍተኛ የካሎሪ እሴት ያላቸው የድንጋይ ከሰል ዓይነቶች ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ተመራጭ ናቸው፡፡ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2021 ኢንተርናሽናል ኢነርጂ ኤጀንሲ ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ የድንጋይ ከሰል በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት አቅሙ በዓለም 37 በመቶ ድርሻ ያለው ከፍተኛው የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጪ አማራጭ ነው።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በዓለም ላይ ከ3ነጥብ6 ሺህ በላይ የድንጋይ ከሰል ተፋሰሶች አሉ። በዓለም ላይ ትልቁ የድንጋይ ከሰል ክምችት በአሜሪካ የሚገኝ ሲሆን፤ አሜሪካ ከፍተኛውን የዓለም የድንጋይ ከሰል ክምችት ማለትም 23 በመቶውን ድርሻ ትይዛለች። 13 በመቶ በመያዝ ሩሲያ የሁለተኛነት ደረጃ የያዘች ሲሆን፤ ቻይና 11 በመቶ የድንጋይ ከሰል ክምችት ያላት ሦስተኛዋ ሀገር ሆና ትከተላለች፡፡

ኢትዮጵያ ከቢሊዮኖች ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ክምችት እንዳላት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለበርካታ ዓመታት ይህን የማዕድን ሀብት መጠቀም አልቻለችም፤ እስከ 2014ዓ.ም ድረስም የድንጋይ ከሰልን ለኢንዱስትሪዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ግብዓትነት ከውጭ ሀገር በውድ ዋጋ እያስገባች ስትጠቀም መቆየቷ ይታወሳል። በዚሁ ዓመትም ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ በማድረግ የድንጋይ ከሰል ከውጭ አስገብታለች፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የድንጋይ ከሰል በማምረት ለኢንዱስትሪዎች የኃይል አማራጭነት ለማዋል ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይሁንና ይህ የድንጋይ ከሰል ምርት ግን ከጥራት ጋር በተያያዘ ተፈላጊነቱ እስከዚህም ነው ሲባል ቆይቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት ሀገር ውስጥ ያለው ድንጋይ ከሰል ጥራት የጎደለው፣ የእርጥበት መጠኑ ከፍተኛ የሆነ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ለሚፈልጉ ፋብሪካዎች የማይሆን ነው እየተባለ ከውጭ ሀገራት ከቱርክ፣ ከቻይና፣ ከደቡብ አፍሪካ እና ከመሳሰሉ ሀገራት የድንጋይ ከሰል እንዲገባ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

ይሁንና የድንጋይ ከሰል ከውጭ ከሚገባው ይልቅ በሀገር ውስጥ የሚመረተው ምርትን የማቃጠል አቅሙ ከፍተኛ መሆኑን በጥናት እንደተረጋገጠ የማዕድን ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል፡፡ ስለሆነም መንግሥት ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት በማስቀረት በሀገር ውስጥ የመተካት ሥራ በመሥራት በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች በማስጀመር ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ እንደ ሀገር የድንጋይ ከሰል ክምችት ያለባቸው መገኛ ቦታ ተብለው የተለዩ አካባቢዎች የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች፣ የኦሮሚያ፣ የአማራ እና የቤኒሻንጉል ጉምዝ ይጠቀሳሉ። በቅርቡ ሕልውናውን ያጣው የቀድሞው የደቡብ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የድንጋይ ከሰል ማዕድን እንዳላቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የድንጋይ ከሰል ምርት ከሚታወቁት አካባቢዎች አንዱ የሆነው የአማራ ክልል ነው፡፡ በክልሉ በጭልጋ ዞን ምስራቅና ምዕራብ ደንቢያ ወረዳዎች ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ ከሰል ክምችት ስለመኖሩ አንድ መረጃ ይጠቁማል፡፡ የድንጋይ ከሰል ክምችቱን አስመልክቶ ከአራት ዓመታት በፊት የጎንደር ዩኒቨርሲቲና ሌሎች የዘርፉ ባለሙያዎች ባደረጉት ጥናት 19 ሚሊዮን ቶን የማዕድን ሃብት እንዳለ በጥናቱ መረጋገጡን የክልሉ የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ መረጃ ይጠቁማል፡፡

በክልሉ የድንጋይ ከሰል ሃብትን ፈጥኖ ወደ ልማቱ በማስገባት ለማዕድኑ ግዢ በየዓመቱ የሚወጣውን ወጪ በማስቀረት ረገድ በትኩረት እየተሰራ ነው። የድንጋይ ከሰል ለማልማት የሚያስችሉ የአሰራር መመሪያዎችና ደንቦችን ከማዘጋጀት ጀምሮ በየደረጃው መዋቅሮችን በመዘርጋት ለአልሚ ባለሀብቶች ፈጣን አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ ተመላክቷል፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታትም አቅምና ፍላጎት ያላቸውን ባለሃብቶች በዘርፉ ለማሰማራት በተደረገው ጥረት በወቅቱ ፍላጎታቸውን ላሳዩ አራት ባለሃብቶች በዘርፉ መሰማራት የሚያስችላቸውን ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ሥራ በሂደት ላይ እንደነበር ተጠቁሟል፡፡

በሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል የሚመረትበት ሌላው ክልል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ነው፡፡ የክልሉ ዳውሮ ፣ ኮንታ እንዲሁም ከፋ ዞኖች በድንጋይ ከሰል ምርታቸው ይታወቃሉ፡፡

የክልሉ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የማዕድን ዘርፍ ኃላፊ አቶ መንገሻ መዳልቾ በክልሉ ያለውን የድንጋይ ከሰል ክምችትና እየተካሄደ ያለውን ልማት አስመልክቶ በቅርቡ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በክልሉ ያለውን የድንጋይ ከሰል ማዕድን ክምችት ለማወቅ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አሁን ላይ ማዕድኑ እየወጣ ያለው በገጸ ምድር እና በከፊል ገጸ ምድር ላይ ያለውን ማዕድን በመጠቀም ነው፡፡

በክልሉ 15 አነስተኛ ደረጃ አምራቾች እና ሦስት በከፍተኛ ደረጃ አምራቾች በአጠቃላይ 18 አምራቾች ፈቃድ ወስደው የድንጋይ ከሰል ወደ ማምረት ሥራ ተገብቶ እየተሰራ መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰው፣ ከክልሉ በ2015 በጀት ዓመት 748 ሺ24 ቶን ያህል የድንጋይ ከሰል ለማምረት ታቅዶ፤ 209ሺ398 ቶን ለማምረት ተችሏል ይላሉ፡፡

ከእቅዱ አንጻር አፈጻጸሙ ውስን ነው የሚሉት ኃላፊው፤ ለዚህም በርካታ ችግሮች መኖራቸውን ነው በምክንያትነት የሚጠቅሱት፡፡ ከገቢም አንጻር 30 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማስገባት ታቅዶ፤ 29 ነጥብ3 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት መቻሉን ይናገራሉ፡፡ በድንጋይ ከሰል ምርት ብቻ ለ600 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ ለ525 ዜጎች ቋሚና ጊዚያው የሥራ እድል መፍጠር መቻሉንም ጠቅሰዋል፡፡



በ2015 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ቶን የድንጋይ ከሰል ተመርቷል

እሳቸው እንዳሉት፤ በ2016 በጀት ዓመት የድንጋይ ከሰል ምርት ሥራውን አጠናክሮ ለማስቀጠል ታቅዷል። በበጀት ዓመቱ 500ሺ ቶን የድንጋይ ከሰል ለማምረት የሚያስችል እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

ከጥራት ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመፍታት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የድንጋይ ከሰል ምርትን መስፈርቱ (ስታንዳርዱን) የጠበቀ ለማድረግ ከምርት ሂደት አንጻርም ዝቅ ሊል እንደሚችል የጠቆሙት ኃላፊው፤ ለዚህም መፍትሔ ለማፈላለግ እየተሰራ ነው ይላሉ፡፡ የድንጋይ ከሰል ፕሮሰሲንግ ማሽን በዳውሮ ዞን በኢትዮ ማይኒንግ ኮርፖሬሽን የመትከል ሂደት እያለቀ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡ ይሄ እየታየ እንደሚሰፋም ተናግረዋል፡፡

የማዕድን ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽንና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አወቀ ተስፋው በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ከግማሽ ቢሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ክምችት አላት፡፡ የድንጋይ ከሰል በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በጂማ፣ በዳውሮ፣ በኮንታ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በከማሼ፣ በአርጆ፣ በጭልጋ አካባቢዎችና በሌሎችም አካባቢዎች ይገኛል፡፡

“ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት ሙሉ ለሙሉ ለመተካት የሚያስችል ሥራ እየተሰራ ነው” የሚሉት የኮሙኒኬሽንና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት ፈቃድ ወስደው የተሰማሩ ኩባንያዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከፌዴራል መንግሥት ስምንት ኩባንያዎች የድንጋይ ከሰል ለማምረት የሚያስችላቸው ፈቃድ መውሰዳቸውንም ያመለክታሉ። ክልሎችም የድንጋይ ከሰል ለማምረት ለሚፈልጉ አካላት ፍቃድ መስጠት የሚችሉበት አግባብ መኖሩን ተናግረዋል፡፡ በክልሎች ፈቃድ ወስደው በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራትና ኩባንያዎች እንዳሉም አመላክተዋል፡፡

ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ የመተካት ሥራው ተጠናክሮ መቀጠሉን ነው ኃላፊው የሚገልጹት፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ በ2015 በጀት ዓመት በሀገር ውስጥ 1ነጥብ2 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ምርት ማምረት ተችሏል፡፡ በዚህ ከ7 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማዳን ተችሏል፡፡ የ2016 በጀት ዓመት ሁለት ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት ታቅዷል፡፡

በሀገር ውስጥ ድንጋይ ከሰል በማምረት ዙሪያ ተግዳሮቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ የድንጋይ ከሰል በሚመረትባቸው ቦታዎች የአለመረጋጋትና የጸጥታ ችግሮች ማጋጠማቸውንም ተናግረዋል፡፡ ይህም በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች በእቅዳቸው መሠረት ወደ ሥራ ያለመግባት ተግዳሮት ሆኖባቸው መቆየቱን ይናገራሉ፡፡

ይህንን ችግር ለመፍታት አሁን ላይ ምርቱ በሚመረትባቸው አካባቢዎች ላይ የጸጥታ አካላት ተሰማርተው ከህብረተሰቡ ጋር እየሰሩ ነው የሚሉት ኃላፊው፤ ኩባንያዎችም ወደ ሥራ እንዲገቡ የመደገፍና የመከታተል ሥራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ነው የገለጹት፡ ፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ በቀጣይም ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ምርት ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየተሰራ ነው። የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ ትልልቅ ኩባንያዎች ወደ ምርት እንዲገቡ ድጋፍ እየተደረገ ነው። ሌሎች ኩባንያዎችም ወደ ዘርፉ እንዲገቡ የሚያደርግ ሥራም እየተሰራ ነው። በሌላ በኩል ከዚህም አልፍ ብሎ የድንጋይ ከሰል ወደ ውጭ ለመላክ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የዛሬው ዋንኛ ርእሳችን የሆነውን የድንጋይ ከሰልን ጨምሮ ኢትዮጵያ እንደ ወርቅ፣ ፖታሽ፣ የብረት ማዕድን፣ የከበረ ድንጋይ፣ ሊቲየም፣ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ያሉ የተለያዩ የማዕድን ሃብቶች አላት። የማዕድን ዘርፍ ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንድ በመቶ ድርሻ እና 14 በመቶ ኤክስፖርት መጠን እንዳለውም ይገመታል። ይህ ዘርፍ የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም ለብዙ ሰዎች የሥራ እድልም የፈጠረ ነው።

መንግሥት የማዕድን ዘርፉን ለማሳደግና ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ የሚያስችል ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ እየሰራ መሆኑንም በተደጋጋሚ ሲገልጽ ይደመጣል። በተጨማሪም የማዕድን ልማት ሥራው አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን የሚያስጠብቅ ብሎም ዘላቂነት ለማረጋገጥ ያለመ ነው። የማዕድን ዘርፉ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን እየተጋፈጠም ይገኛል፡፡ የመሠረተ ልማት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ጉድለቶች ከተግዳሮቶቹ መካከል ይጠቀሳሉ። የአካባቢ መራቆት፣ ግጭት እና ሕገወጥ ንግድም ሌሎች ዘርፉን የሚፈትኑ ችግሮች ናቸው።

መንግሥት የዘርፉን ፋይዳ በማጤን በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት መሪ እቅድ አምስት ምሰሶዎች ካላቸው ውስጥ ማዕድንን አካቶት እየሰራ ይገኛል፡፡ መንግሥት ተኪ ምርቶችን በማምረት የውጭ ምንዛሬ ለማዳን እያከናወናቸው ከሚገኙ ተግባሮች መካከል የድንጋይ ከሰል ምርትን በሀገር ውስጥ ለማምረት እየተከናወነ ያለው ተግባር ይጠቀሳል። በአሁኑ ወቅትም ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እየተቻለ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር መረጃ ይጠቁማል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ጥሳ

በትረ ሙሴ (መልከ ሊትዮጵ)

ነፍስ ጥላ ናት... ከዚህ ወደዛ መራመጃ፡፡ ብዙ ደክሞኝ የማርፈው በፈገግታዋ ጥላ ውስጥ ነው፡፡ ማንንም የሚያሳርፍ የደግነት ጥላ አላት፡፡ ምን እንደሆንኩ አልነግራትም መከራዬን ላጋባባት ስለማልፈልግ ደህና መስዬ እታያታለሁ፡፡ መኖር አባዝኖኝ፣ ሕይወት አንከራቶኝ እየሳኩ መጥቼ ጉያዋ ውስጥ አርፋለሁ። የሴት ነፍስ የወንድ ልጅ ከዘራው ናት፡፡ አጎብድዶ መጥቶ ቀና ብሎ የሚሄድባት፡፡ አለመኖሯን ሳስብ እፈራለሁ። እሷ ባትኖር የሚሆነውን ለማሰብ ድፍረት አግኝቼ አላውቅም። ብዙ እልልታዎቼ ከእሷ መኖር ውስጥ ያገኘኋቸው ናቸው፡፡ ብዙ ምስጋናዎቼ በእሷ መኖር የተቀበልኳቸው ናቸው፡፡ አለመኖሯ ያስፈራኛል..ማሰብ የማልፈልገው ብፈልግ እንኳን ጀምሬ የማልጨርሰው የእሷን በእኔ ውስጥ አለመኖር ነው፡፡

ባትኖር የምሆነውን መገመት አልችልም፡፡ በእሷ በኩል ፈሪ ነኝ፡፡ ማንም የሚጎዳኝ በእሷ በኩል ነው። ብዙ የመከራ ፀሐዮችን፣ ብዙ የሕይወት ጠራራዎችን ተከልዬባታለሁ፡፡ የነፍሴ ጥላ ናት... ሀሩርና ብርዱን ያለፍኩባት..

ከድባቴ የሚያነቃ ከሞት የሚቀሰቅስ የሚመስል ሳቅ አላት፡፡ ከዘላለም እስከዘላለም እንደገደል ማሚቱ በጆሮ ላይ የሚያረብብ ሳቅ፡፡ የእየሱስን ድምጽ ሰምተው እንደለመለሙት ሣሮች፣ አፋቸውን ለዝማሬ እንደከፈቱት የቢታንያ ድንጋዮች ሳቋን ሰምቶ ማንም ዝም ማለት አይችልም፡፡ አባዬ ስትለኝ ያን ጊዜ ነው ሞትን የምንቀው።

እሷን ከምትመስል ሴት ነው የወለድኳት፡፡ በልጄ ውስጥ ቀይ ረጅም ሴት፣ ፀጉሮቿን ጀርባዋ ላይ የምትለቅ፣ ፒጃማ የሚያምርባት ሴት ትታወሰኛለች፡፡ ዝግ ብላ የምታወራ... ብዙ ቁጣዎቼን በትዕግስት አልፋ ባሏ ያደረገችኝ ሴት፡፡ በግራ ድዷ ላይ ድርብ ጥርስ ያላት... ስትስቅ መላዕክቶች የሚቀኑባት፣ ወጥቼ ስዘገይ አስር ጊዜ የምትደውል፣ ውጭ ቆማ የምትጠብቀኝ ሴት ትታወሰኛለች፡፡

### ሀሳብ ወሰደኝ..

እለተ ሰኞ... ረፋዱ ላይ አረፋፍጄ ከእንቅልፌ ነቃሁ። ቁርስ በልቼ ነፍሰ ጡር ሚስቴን ግንባሯ ላይ ስሜ ከቤት ወጣሁ። ስወጣ ተሰምቶኝ ከማያውቅ ከሆነ ባዶነት ጋር ነበር፡፡ ሃሳቤ ውስጥ እየተሰነቀረ የሚረብሽ የሆነ ሃሳብም አብሮኝ ነበር፡፡ ከቤት እንደወጣሁ ቀጥታ ወደሥራ ነበር የሄድኩት፡፡ ልቤ አላረፈም..ምን እንደሆንኩ ሳላውቅ ይጨንቀኝ ጀመር፡፡ በዛ ጠዋት ከሚስቴ ‹ሰላም ገባህ? ቀጥሎ እናቴ ነበረች የደወለችልኝ፡፡ እናቴ የሆነ ነገር ልትነግረኝ ፈልጋ እንዳልነገረችኝ በድምጽዋ ተረዳሁ። ምን ሆነሻል! ደህና አይደለሽም እንዴ? አልኳት ደም ብዛቷ ተነስቶ ከሆነ ብዬ፡፡

‹ጥሩም ህልም አላየሁ ብቻ ፈጣሪ ያውቃል.. ‹አንቺ ደግሞ በሆነ ባልሆነው መጨነቅ ትወጃለሽ› ብዬ ሰላም ዋይ ብያት ተለያየን፡፡ የእናቴ ሁኔታ ሲሰማኝ ከነበረው ስሜት ጋር መገጣጠሙ የእውነት እንድፈራ አደረገኝ፡፡ አንዳንድ ቀኖች ነገን የሚናገር አንደበት አላቸው የሚለው የእናቴ የዘወትር ንግግር ታወሰኝ፡፡ እናቴ በምታምነው በዛ ቀን ላይ ከእንቅልፌ እንደነቃሁ አመንኩ፡፡ ቀኑን እንዲችው ስጨነቅ ዋልኩ፡፡ ከአሁን አሁን አዲስ ነገር ተከሰተ እያልኩ ስሰጋ ቀኑ መሸ፡፡ ማታ እንደ ጠዋት አይደለም። ጠዋት የተስፋ መብቀያ ነው ማታ ደግሞ መድረቂያ። ሲመሽ ፈሪ ያደርጋል፡፡ ንጋት እንጂ ምሽት አቅም ይሰልባል። አቅሜ ተሰልቦ ወደቤት ገባሁ። ማታ ቤት ስገባ ምንም የተለየ ነገር አልነበረም፡፡ ሁሉም ነገር እንደነበረ ሆኖ ጠበቀኝ፡፡ ሚስቴ እንደወትሮዋ በር ላይ እየጠበቀችኝ አገኘኋት፡፡ ግንባሯን ስሜ ተቃቅፈን በነፍሰ ጡር ርምጃ ቤት ገባን፡፡ ዝም ብዬ እንደተጨነኩ ሳስብ በሞኝነቴ ሳኩ፡፡

ራት በላን፡፡ ስለምትወለደው አዲሷ ልጃችን አውርተን፣ ስለሚወጣላት ስም የፍቅር ጭቅጭቅ ተጨቃጭቀን...ትራስ ተወራውረን ወደመኝታችን ሄድን። መኝታ ክፍል ስንደርስ እጄን ለቀም አድርጋ ‹እቀፈኝ! አለችኝ፡፡ እንኳን እቀፈኝ ተብዬ ወትሮም እሷን የማቀፍ ሱሰኛ ነኝ እንደተባልኩት ሆዷን በማይጎዳ መልኩ አቀፍኳት፡፡ ዛሬ አንተኛም... እያወራን እንድናድር እፈልጋለሁ› አንሾካሾከችልኝ፡፡

‹ማረፍ አለብሽ ባይሆን ነገ ከሥራ ቀርቼ እያወራን እንውላለን› አልኳት፡፡

እሺም እምቢም ሳትለኝ ትክ ብላ አስተዋለችኝ፡፡

‹ለምንድነው እንዲህ የምታይኝ?

እያየችኝ አይኖቿ እንባ ሲያመነጩ አየሁ፡፡ ‹ምን ሆነሻል?

‹እናቴ እኔን እንደወለደች ነው የሞተችው› አለችኝ፡፡

‹እሱን አውቃለሁ! ታዲያ ይሄ ካንቺ ጋር ምን ያገናኘዋል? ዝም ብለሽ ራሽን አታስጨንቂ› ስል በቀስታ ወደ አልጋው ጎተትኳት፡፡

‹ፈራሁ..! አለችኝ፡፡

አይዞሽ በሚመስል እቅፍ አደረኳት፡፡ ዝም ብላኝ ወዳልጋው ሄደች፡፡ የእናቴ የስልክ ጥሪ ሁለታችንንም ከሃሳብ መነጠቀን፡፡ ስልኩን ማንሳት ፈራሁ፡፡ ቀን ሙሉ የተጨነኩበት ስልክ አሁን ደግሞ ምን ሊነግረኝ ነው?

‹ስልኩን አንሳው እንጂ..! የሂሩት ድምጽ ተሰማ፡፡

‹መልሼ እደውልላታለሁ› አልኳት፡፡

ተቃቅፈን ተኛን..

ከሁለት ቀን በኋላ ሥራ ቦታ እያለሁ የማላውቀው አንድ ስልክ ተደውሎልኝ ሆስፒታል ድረስ ተባልኩ፡፡ የተባልኩት ሆስፒታል ስደርስ ሂሩትን ሬሳ ማቆያ ክፍል ሲወስዷት ከመንገድ ተገናኘን፡፡ ሂሩት የሞተችበት ሆስፒታል ውስጥ ራሴን ስቼ አስራ አምስት ቀን ተኛሁ። ከረጅም ጊዜ ራስን መሳት በኋላ ከሴት ልጄ ጋር ተዋወኩ። ሂሩት እንደ እናቷ የመጀመሪያ ልጃችንን ወልዳ ነበር የሞተችው፡፡ ሂሩትን ካጣሁ እንሆ ሰባት ዓመታት ተቆጠሩ፡፡

ከሃሳቤ መልስ ወደ መና አየሁ... ክንዴ ላይ አንቀላፍታለች። እንደ እናቷ ናት... ከእኔ የወሰደችው አንድም ነገር የለም፡፡ ሂሩት አንድ ሳታስቀር ራሷን ነው የሰጠችኝ፡፡ እግዜርን የታረኩት ሚስቴን በምትመስል ልጄ በኩል ነው፡፡ ሚስቴን ወስዶ ሚስቴን ሰጠኝ፡፡ ልጄን አግብቼ የምኖር ነኝ፡፡

መና የሚለውን ስም ያወጣችላት ሂሩት ናት፡፡ ሁሌ ማታ ማታ በልጃችን ስም በኩል የፍቅር ጭቅጭቅ እንጨቃጨቅ ነበር። እኔ ግን ሂሩት ነው የምላት። የሚስቴን ስም ለልጄ ሰጥቼ... በሚስቴ ስም ልጄን እጠራለሁ፡፡ አዳልጦኝ መና ብያት አላውቅም። ግን አሁንም አለቅሳለሁ፡፡ ሂሩትን ለማስረሳት ልጄ ብቻ በቂ ናት አልልም፡፡ እግዜር እንዴትም ቢባርከኝ ስለሂሩት መጽናኛ የማገኝ አይመስለኝም፡፡ ባሰብኩት ቁጥር ሁሌ የሚያስለቅሰኝ ለእኔ ስትል ዶክተር ልጅሽን ስትወልጂ ትሞቻለሽ ያላትን ደብቃ ለብቻዋ ተሰቃይታ መሞቷን ሳስብ ነው፡፡

የምኖረው ትላንትን ነው፡፡ ዛሬ ላይ ያለሁ እመስላለሁ እንጂ ትላንትን ነው የምኖረው፡፡ ሳቁ እና ታሪኬ ከትላንት ተመዞ ዛሬን ያደመቀ ነው፡፡ ሂሩት የነበረችበት ትላንት ሁሉ ይናፍቀኛል... በምንም አልቀይረውም፡፡ እሱን ብሎ ወንድ የሚሉትን እኔን ነው ከመሬት አንስታ ባሏ ያደረገችው... ለዛውም በብዙ ፍቅርና ጥሩነት፡፡

መቼም እንዳልበረታ ከእሷ ዘንድ የነፈሰ ንፋስ ነፍሴን አጠውልጓታል፡፡ መቼም እንዳልሽር፣ መቼም እንዳልቆም ያደረገኝ ትዝታ በእኔ ውስጥ አለ፡፡ እንደ ሸረሪት ድር የተጠላለፈ ከእኔ ውጭ ውሉን የማያውቅ፣ ከእሷ ውጭ ውሉን ያልደረሰበት የፍቅር ውርስን ተወራርሰናል። በልጄ ነፍስ ውስጥ ግን አያታለሁ... አልሞተችም ሞታለችም፡፡ ልጄ ሚስቴም ልጄም ናት... አንድ ነፍሷን በሚስትነት እና በልጅነት አፍቅሬው የምኖር ነኝ፡፡

በሂሩት ሞት ላይ እግዜር ቢሳሳት... እሷን መች አልኳችሁ? ብሎ መላዕክቶቹን ቢቆጣ... ሂሩትን ለዳግም ሕይወት እድል ቢሰጣት ስል እብድ የማያስበውን ሃሳብ አስባለሁ፡፡ ወደፊትም እንዲህ ነኝ... በዛሬና በነገ የምዳክር..

# ዓለም አቀፍ

## አውስትራሊያ እንደ አዋቂ ሳሰረቻቸው ታዳጊዎች 17 ሚሊዮን ዶላር ለመክፈል ተስማማች

በጋዜጣው ሪፖርተር



በአውስትራሊያ ከ120 በላይ የሚሆኑ ኢንዶኔዥያውያን ታዳጊዎች እንደ አዋቂ ታስረዋል በሚል በመንግሥት ላይ በቀረበው ክስ አሸናፊ ሆነው ካሳ እንዲከፈላቸው ተወሰነ።

የአውስትራሊያ መንግሥት ለእስር ለተዳረጉት እንዲሁም ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ናችሁ በሚል ክስ ለቀረበባቸው ታዳጊዎች 17 ሚሊዮን ዶላር ካሳ ለመክፈል ተስማምቷል።

12 ዓመት ያልሞላቸው ሕጻናትን ጨምሮ በርካታ ታዳጊዎች በእስር ላይ እንደነበሩም ተመልክቷል።

አውስትራሊያ ካላት ጥገኝነት ጠያቂዎችን ከሚመለከት ፖሊሲዎች ጋር በተያያዘ ተከታታይ ክሶች እየቀረቡ ባለበትም ወቅት ነው እዚህ ስምምነት ላይ የተደረሰው።

“በውጤቱ በጣም ተደስተናል። ይህንን ከጀመርን አስር ዓመታት አልፈዋል” ሲሉ ከታዳጊዎቹ ጠበቆች አንዱ ሳም ቲየርኒ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

በአውስትራሊያ መንግሥት ላይ ክስ ያቀረቡት አብዛኛዎቹ ታዳጊዎች በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች አማካኝነት በጀልባ ወደ -ሀገሪቱ ከገቡ በኋላ በአውሮፓውያኑ 2009 እና 2012 መካከል ለእስር ተዳርገዋል።

ታዳጊዎቹ ታስረው የነበረው በክሪስማስ እና በዳርዊን ደሴቶች ላይ እንደሆነም ተነግሯል። ታዳጊዎቹ በጀልባዎቹ በመሳፈር ወደ አውስትራሊያ ያቀኑት ከፍተኛ ገንዘብ የሚከፈልበት ሥራ እንደሚያገኙ እንዲሁም አንዳንዶቹ መድረሻቸውን ሳያውቁ በአዘዋዋሪዎች ተታለው ነው ተብሏል።

በአውስትራሊያ ሕግ መሠረት በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገሪቱ የገቡት ታዳጊዎች ወደ መጡበት ሊመለሱ ይገባ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ሀገሪቷ ባስቀረችው ኤክስሬይ ምርመራ አማካይነት ባለሥልጣናቱ ታዳጊዎቹ ከ18 ዓመት በላይ እንደሆኑ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል ተብሏል።

ጉዳዩን ይፋ በማድረግ እና እንዲጣራ ከረዱት መካከል የእስር ቤት ጠባቂዎች አንዱ ኮሊን ሲንገር ነው። ጠባቂው በአውሮፓውያኑ 2018 ለቢቢሲ እንደተናገረው የአውስትራሊያ መንግሥት “ሕጻናቱን ዕድሜያቸውን አውቆ ሆን ብሎ እንዳሰራቸው” አጋልጧል።

የኢንዶኔዥያ መንግሥትም ታዳጊዎቹን ለመርዳት “ምንም ማድረግ አልፈለገም” ሲልም ጠባቂው ተናግሮ ነበር። የአውስትራሊያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የታዳጊዎቹ መብቶች እንደተጣሱ እና ጉዳያቸውም በስህተት ተይዞ እንደነበር በሪፖርቱ አውጥቷል።

በመንግሥት ላይ ክስ ካቀረቡት አንዱ የሆነው አሊ ጃስሚን በጉዳዩ ላይ የተሳተፉ የአውስትራሊያ ባለሥልጣናትን በቸልተኝነት እና በዘር መድልዎ ከሷቸዋል።

## አሜሪካ ከኢራን የያዘቻቸውን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጥይቶች ለዩክሬን ሰጠች

በጋዜጣው ሪፖርተር



አሜሪካ ባለፈው ዓመት ከኢራን የያዘችውን አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ጥይቶች ለዩክሬን መስጠቷን ጦሯ አስታወቀ።

በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠረው የአሜሪካ ማዕከላዊ ዕዝ (ሴንትኮም) እንዳለው ጥይቶቹ ታኅሳስ ወር ላይ ወደ የመን ሲጓዝ ከነበረ መርከብ ላይ የተወረሱ ናቸው።

በቅርቡ ዩናይትድ ኪንግደም እና የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) የምዕራቡ የጦር ኃይሎች ዩክሬን ከሩሲያ ወረራ ራሷን እንድትከላከል የሚያቀርቡት ጥይት እያለቀባቸው እንደሆነ አስጠንቅቀው ነበር።

ማዕከላዊ ዕዙ እንዳለውም እነዚህ የኢራን ጥይቶች ሰኞ ዕለት ወደ ዩክሬን ተልከዋል። የአሜሪካ መንግሥት ሐምሌ ወር ላይ የእነዚህን ጥይቶች ባለቤትነት ያገኘውም ‘ሲቪል ፎርፌቸር’ በሚባለውና የንብረቱ ባለቤት በወንጀል ድርጊት ውስጥ ተሳትፏል ተብሎ የሚታመን ከሆነ ንብረቱ እንደሚወረስ በሚፈቅደው አሠራር ሂደት ነው።

ንብረትነቱ የኢራን የታጠቁ ኃይሎች አካል የሆነውና የሀገሪቷን መንግሥት የሚጠብቀው የኢራን እስላማዊ አብዮት ጠባቂ ወታደሮች እንደሆነ ይታመናል።

ዕዙ በሰጠው መግለጫ፣ አሜሪካ በቀጠናው በማንኛውም ሕጋዊ መንገድ የኢራንን የመሣሪያ ድጋፍ ለመቆጣጠር ከአጋሮቿ እና ከተባባሪዎቿ ጋር ለመሥራት ቁርጠኛ ናት ብሏል።

በየመን እየተካሄደ ባለው የእርስ በርስ ጦርነት ኢራን የሁቲ አማጺያንን ትደግፋለች። ነገር ግን የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት የ2015 ውሳኔ መሠረት ለቡድኑ መሣሪያ ማቅረብ ክልክል ነው።

በየመን ያለው የእርስ በርስ ጦርነት በአውሮፓውያኑ 2014 የተጀመረ ሲሆን የሁቲ አማጺያን መዲናዋን ሰንዓን ተቆጣጥረው የሀገሪቷን መንግሥት አስወግደዋል።

ከሥልጣን የተወገደው መንግሥት ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ሲሆን በሳዑዲ በሚመራውና በቀጠናው ባሉት ሀገራት ጥምረት እንዲሁም በአሜሪካ እና በዩናይትድ ኪንግደም ይደገፋል።

ከባለፈው ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ኢራን በዩክሬን ላለው ጦርነት ለሩሲያ መሣሪያ በተለይም ደግሞ ሰው አልባ አውሮፕላን (ድሮን) በማቅረብ በተደጋጋሚ ተከሳለች።

ሰኞ ዕለት ምዕራባውያኑ ለዩክሬን ስላቀረቡት ጥይቶች በዋርሶው የጸጥታ ፎረም ላይ የኔቶ ጦር ኮሚቴ ሰብሳቢ አድም ሮብ ባወር “አሁንም ቋቱ አልሞላም” ብለዋል።

ሰብሳቢው እንዳሉት በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ የኔቶ አባል ሀገራት የጥይት ክምችት በግማሽ ያለቀ ወይም ባዶ ነበር። “ለ30 ዓመታት በጋራ የገነባነው ነጻ ኢኮኖሚ ለብዙ ነገር መልካም ነው። የታጠቁ ኃይሎች ይህ የላቸውም” ብለዋል።

ጨምረውም መንግሥት እና የጦር መሣሪያ አምራቾች በከፍተኛ ሁኔታ ምርታቸውን መጨመር እንደሚጠበቅባቸውም ተናግረዋል።

የዩናይትድ ኪንግደም መከላከያ ሚኒስትር ጀምስ ሂፒይ የኔቶ አጋሮች የሀገራቸውን ገቢ ሁለት በመቶ በመከላከያ ላይ ማዋል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

አባል ሀገራቱ በዚህ ላይ የተስማሙ ቢሆንም ከ31ዱ አባል ሀገራት በዚህ ዓመት ግቡን ያሳካሉ ተብሎ የሚጠበቀው11ዱ ብቻ ናቸው።

# ነፃ ሃሳብ

# ኤሬቻ የምስጋና የፍቅር እና የአንድነት በዓል

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ኤሬቻ የምስጋናና የአብሮነት በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት፣ አምላኩን የሚያመሰግንበት የምስጋና ክብረ በዓል ነው፡፡ በማህበረሰቡ ወግና ሥርዓት በሚመራ የአባቶች ምርቃትና ቡራኬ የመስቀል በዓልን ተከትሎ በመዲናችን አዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፣ በቢሾፍቱ ከተማ ደግሞ የሆራ ሀር ሰዲ ከፍተኛ ሕዝብ በታደምበት ይከበራል፡፡ ላለፉት አምስት ዓመታት ባህላዊ እሴቱን ሳይለቅ እንዲህ ባለው የጋራ መንፈስ ሲከበር ሰንብቷል፡፡

ኤሬቻን በትክክል ሊገልጹት ከሚችሉ ሃሳብና ቃላት መካከል የመጀመሪያው ‹የምስጋና በዓል› የሚለው ነው፡፡ መነሻና መድረሻውን ምስጋና ያደረገው ኤሬቻ በማኅበረሰቡ ዘንድ አንድነትን ፈጥሮ ስለሀገርና ሕዝብ የሚጸለይበት የተማጽኖ እሴት ነው፡፡ ከዚህ እውነት በመነሳት ኤሬቻ ፍቅር፣ አንድነት እና ወንድማማችነት የሚጸኑበት የእርቅና የተግባቦት ሥርዓት መሆኑን ለመረዳት አይከብድም፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ በታሪክ ተመራማሪነታቸው አንቱታን ያተረፉ እንደ ዲሪቢ ደምሴ እና ገመቹ መገርሳ (ዶ/ር) የመሳሰሉ ምሁራኖች ገለጻ፣ ኤሬቻ ማለት ዋቃ ‹ፈጣሪ› ማለት ነው ፤ የክብረ የበዓሉ አላማም ይሄን ፈጣሪ ማመስገን ነው ፡፡

በዓሉን ከጨለማ ወደብርሃን ወይም ደግሞ ከመንጋት ጋር የሚያይዙትም አሉ፡፡ ከክረምት መገባደድ በኋላ የኤሬቻ በዓል የሚከበርበት ዋነኛው ምክንያት ትናንትን ላሳለፈን፣ ጨለማውን ላሻገረን፣ ክረምቱን ወደበጋ የለወጠ ፈጣሪ ምስጋና መቸሪያ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ጠቅለል ሲደረግ የኦሮሞ ሕዝብ ሰማይና ምድርን ለፈጠረው ለሁሉ ጌታ ፈጣሪው ‹ዋቃ› ክብርና ምስጋና ለመቸር ሲል የሚያከብረው በዓል ነው፡፡

የኤሬቻ በዓልን ለማክበር የሚመጣ ታዳሚ እንደ ሳርና አበባ ያሉ እርጥብ ነገሮችን ይዞ ይመጣል። ይሄም ‹አንተ ያጸደከው ነው አብቦ ያፈራው› በሚል ሃሳብ የፈጣሪን በጎነት እያሰበ አሜን የሚልበት ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ኤሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደህንነት፣ ፍቅርና አብሮነት የሚለምንበት የተማጽኖ በዓልም ነው ፡፡

ኤሬቻ ከምስጋና ጎን ለጎን የዘመን መለወጫም በዓል ነው፡፡ በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደሚከበረው የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ ማለት ነው፡፡ በክረምት ወራት ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ በአዲስ ዓመት መጀመሪያው መስከረም ላይ ይገናኛል፡፡ ማኅበረሰቡም ክረምቱን በሰላም ላሳለፈ ፈጣሪው ምስጋና ያቀርባል፡፡

አባገዳዎችና ሀዳ ሲንቄ በኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ደምቀው፣ የበዓሉ ተሳታፊዎችም ሥርዓቱን በሚያጎሉ የተለያዩ አይነት የጸጉር አሰራርና መዋቢያ አምረው ሲመርቁና ሲመረቁ ሲያመሰግኑና ሲመሰገኑ ማየት በእውነቱ ደስ ይላል፡፡

ኤሬቻ እና የገዳ ሥርዓት የአንድ ሳንቲም ሁለት መልኮች ናቸው፡፡ ተወራርሰውና ተሰባጥረው ከትናንት ወደዛሬ የመጡ የሥርዓትና የምስጋና ጥምረቶች ናቸው፡፡ የገዳ ሥርዓት ሁሉን አቃፊ የእርቅና የሰላም የአብሮነትም ሥርዓት እና እሳቤ ነው፡፡ ኤሬቻ ደግሞ የምስጋና በዓል፡፡ እኚህ ሁለት የሥርዓትና የውዳሴ ጥምረቶች ከሁሉም ለላቀው ፈጣሪ ቅድሚያ ሰጥተው ኤሬቻ በሚል ስም የፈጣሪ የምስጋና ቀን ላይ አርፈዋል፡፡

መስከረም በርከትከት ያሉ በዓላት የሚከበሩበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በተለየ መልኩ የዘንድሮው አዲስ ዓመት በርከት ያሉ የአደባባይ በዓላትን አሳይቶናል። የአደባባይ በዓላት ፍቅርንና አንድነትን፣ እርቅንና ሰላምን ከማውረድ ጎን ለጎን ታሪክን የሚያድሱ፣ አብሮነትን የሚመልሱ ናቸው፡፡ እንዲህ አይነት ሀገራዊ በዓላት በአሉባልታና መሰረት በሌለው ወሬ መደብዘዝ የለባቸውም፡፡

መልካም እሴቶች ሀገርና ትውልድ ማነጫዎች ናቸው፡፡ ከክብረበዓልነት ባለፈ ትውልዱ ልብ ውስጥ ገብተው ፍቅርና ትህትናን፣ አንድነትንና ይቅርባይነትን ቢያስተምሩት ለመነጋገርም ሆነ ተግባብቶ አብሮ ለመኖር ሃሳብ አናጣም ነበር። ገዳ የሥርዓት ቤት ነው፡፡ ፍቅርን አስቀድሞ አንድነትን ያስከተለ አስተሳሰብ፡፡ ኤሬቻ ደግሞ ከዚህ ስርዐት ውስጥ የተጸነሰ የምስጋና ክብረበዐል። ሁለቱም አሁን ላለችው ኢትዮጵ ያስፈልጓታል፡፡ በገዳ ወደፍቅር እንሄዳለን በኤሬቻ ከፈጣሪ ጋር እንታረቃለን፡፡

ትግላችን እኮ ፍቅር የሚያውቅ ትውልድ መፍጠር ነው፡፡ ትግላችን እኮ በምክክር ሰላሙን ያጸና ማህበረሰብ መስራት ነው፡፡ ታዲያ እንዲህ ያሉ ሰላም እና ፍቅርን ምስጋናንም ሰባኪ እሴቶች ኖረውም ካልተጠቀምንባቸው ልፋታችን ምን ይረባናል? መጀመሪያ ያሉንን እንወቅ፡፡ መጀመሪያ ባሉን እንድመቅ፡፡ ያሉንን እሴቶች በአግባቡ መጠቀም ከቻልን ከምንም በላይ ሰላም ፈጣሪዎች መሆን እንችላለን ።

ሥርዓት የጥበብ መጀመሪያ ነው፡፡ ሥርዓት በሌላት ሀገር ላይ ጥበብ ቤቷን አትሰራም። ጥበብ ቤቷን እንድትሰራ ትውልድ ቀራጭ፣ ማኅበረሰብ አናጭ በጎ እሴቶች ያስፈልጉናል፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊነት ጨዋነት የጀመረባቸው ብዙ መልካም እሴቶች አሉን። እያንዳንዱ ብሄረሰብ ግብረገብነትን የተማረበት የጨዋነት መክሊት አለው፡፡ ኢትዮጵያዊ የሆንው በዚህ ውስጥ ነው። ግብረገብነትን ባስቀደመ ከስም ሁሉ ባማረው አብሮነት ውስጥ የቆምነው በዚህ በኩል ነው፡፡

እንደሀገር ትልቁ ድክመታችን ያሉንን አለማወቃችን ብናውቅም አለመጠቀማችን ነው። ያሉንን በበጎ መንፈስ ከተቀበልን በቂዎቻችን ናቸው። የሌሉንን ከምንሻ ወዳሉን ማየቱ ሀገር ከማቅናት አኳያ የተሻለ አቅምን ይፈጥሩልናል። ኤሬቻ ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ይነሳ እንጂ መሰረቱ ኢትዮጵያዊነት ነው። ፍቅርና አንድነትን ይቅርባይነትንም የምንባባልበት የሁላችን የጋራ በዓል ነው፡፡ ሌሎች በዓላትም ተመሳሳይ መልክ ያላቸው ናቸው። በኢትዮጵያዊነት ጀምረው በኢትዮጵያዊነት የሚያበቁ፡፡

ታሪክ ከየትም ይነሳ በጎ እስከሆነ ድረስ የሁላችን ነው፡፡ መልካም እሴቶች የማንም ይሁኑ እስከጠቀሙን ድረስ የጋራችን ናቸው፡፡ እንደ አስታራቂ በዓላት ያሉ ከግለኝነት የምንወጣበት፣ እውነት የጸነሰው ስለፍቅር የሚለፋ የጋራ ታሪክ ያስፈልገናል፡፡ የማይጥሉን..ከወደቅንም የሚያነሱን፣ የትናንትን እዳ ፍቀው ዛሬን ፍቅር የሚያስተምሩ፣ ወደ ነገ የሚወስዱ የአንድነት ምርኩዞች ያስፈልጉና።

ሀገር ማለት የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች አስተሳሰብ፣ ታሪክ፣ ባህልና ወግ ሥርዓትም ጭምር ነው የሚል የቆየ መረዳት አለን፡፡ እንዳረዳዳችን የሆነ የኑሮ ዘይቤ ግን የለንም፡፡ አንዳንድ ጅብ የሚገባባቸውን ሰፋፊ ቀዳዳዎች የሚፈጥሩት እንዲህ ያሉ ክፍተቶች ናቸው፡፡ እንደአረዳዳችን የሆነ የኑሮ ዘይቤ አብሮነትን ለማስቀጠል ወሳኙ መንገድ ነው፡፡

በዓላት ዘርፈ ብዙ መልክ አላቸው፡፡ በእያንዳንዱ ብሄረሰብ ጉያ ውስጥ ያሉ ወግና ሥርዓቶች የሆነ ጠቃሚ መነሻ አላቸው፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ኤሬቻም ፈጣሪን ማመስገኛ ነው። ፈጣሪን ማመስገኛ ብቻ ብለን የምናበቃው ግን አይደለም፡፡ በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ላይ ከፊታችን ላሉ አስራ ሁለት ወራትና 365 ቀናቶች ፈጣሪን አደራህን የምንልበት፣ ስለሀገራችን፣ ስለሕዝቡ፣ ስለእንስሳቱ የምንጸልይበት፣ በአንድነትና በአብሮነት የምንጸናበት የአዲስ ተስፋ ጅማሬም ነው፡፡

ኤሬቻ ሰፊ ነው..በእድሜው እንኸርርግ..አንቱ ነው፡፡ ሲያስታርቅና ሲያመሰግን፣ ሲመርቅና ተስፋ ሲሰጥ ከርሟል፡፡ አሁን ደግሞ ከአንድ ብሄረሰብ በአልነት አልፎ ሀገራዊ ቀለም ያለው ሆኖ እየተከበረ ይገኛል፡፡ እኛም እንዳለፈው ጊዜ አዲሱን ዓመት በአባቶች ምርቃት በአዲስ ልብ የምንጀምርበት፣ መጠላላትን ትተን በአብሮነት የምንቆምበት እንዲሆን በቀናነት ልናከብረው ግድ ይለናል፡፡

ከቱሪዝም እና ከገጽታ ግንባታ አኳያም እንዲህ ያሉ የአደባባይ በዓላት ሚናቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ አብሮነትን ከመፍጠርና ወንድማማችነትን ከማጽናት አኳያ የማይናቅ ሚና አላቸው፡፡ ኢትዮጵያዊነት ትስስር ነው ስንል ዝም ብለን አይደለም በምክንያት ነው፡፡ የብዙሃነትን ቅይጥ ቀለም የፈጠሩልን ባህልና ወጎቻችን እንዲህ ካለው የአደባባይ በዓል የሚነሱ ናቸው፡፡ የሁላችን ያለፈ ዳና በብዙሃነት ባህልና ሥርዓት የደመቀ ነው፡፡ ማናችንም ለብቻችን ቆመን አልደመቅንም፡፡ ድምቀቶቻችን የሕዝብ በዓላት ናቸው፡፡

በዓላት ትስስር መፍጠሪያ ገመዶች ናቸው። እንዳንላላ ሆነን የጠበቅነው፣ እንዳንወይብ ሆነን የጸናነው እንዲህ ባለው የጋራ ሥርዓት ነው፡፡ አንዱ የአንዱን በዓል ሲያከብር መለያየት እየጠፋ ኢትዮጵያዊነት እየጎላና እየደመቀ ይሄዳል፡፡ አሁን ላለው ሕዝባዊ መንፈስ አንድነትን ከሚፈጥሩ የትስስር ገመዶች ውስጥ እንደ ኤሬቻ ያሉ በዓላት ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ በጋራ ለመቆም የጋራ ሥርዓት ያስፈልገናል፡፡ በአብሮነት ለመጠራት ብቻነት የሌለው ኢትዮጵያዊ መንፈስ ያሻናል፡፡

ኤሬቻ ለኦሮሞ ማኅበረሰብ የምስጋና በዓል ከሆነ እንደሀገር ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ መረዳት ይከብዳል ብዬ አላስብም፡፡ ለምስጋና ሩቅ ለሆነ ማኅበረሰብ፣ ከመተቻቸትና ከመናናቅ ላልወጣ ትውልድ የምስጋና በዓል መኖሩ እንደ አንድ ትልቅ እድል ልንወስደው የሚገባ ነው፡፡

አብዛኞቹ ልዩነቶቻችን ወደሌላው ከማያዩ አይኖቻችን የተነሱ ናቸው፡፡ ምስጋና ሌላውን የምናይበት፣ ስለሌላው የምንጨነቅበት ሀገር መፍጠሪያ ልማድ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት በጎ ልማዶች ዳብረውና ሰፍተው ስንመራረቅና ስንወዳደስ ነው የጋራ ታሪክ የምናበጀው፡፡

ከሆነ ብሄረሰብ በቅለው በጋራ የሚከበሩ እልፍ የአደባባይ በአላት አሉን፡፡ ከሰሞኑ እንኳን ጊፋታን፣ ያዮዴን፣ ዮ መስቃላን አክብረናል፡፡ በቀጣይም የምናከብራቸው ይኖራሉ፡፡ እኚህ ባህሎች የአንድ ወገን ይመስላሉ እንጂ አይደሉም፡፡ ከሁላችን በሁላችን የሁላችን ናቸው፡፡ አዲሱ ትውልድ በእንዲህ ባለ አንድነትንና አብሮነትን በሚያጠነክር የጋራ በዐል ካልታነጸ በምንም ቢበረታ መዛሉ የማይቀር ነው፡፡

አሁን ላይ ከየት እንደለመድናቸው ብንጠየቅ መልስ የማናገኝላቸው ከኢትዮጵያዊነት የሚያርቁ አንዳንድድ የብቻነት ልማዶች እየተጠናወቱን ነው። ከለመድነውና አቅፎ ከያዘን ሰፊ እጅ ሸሽተን መድረሻችን የት እንደሚሆን ለማወቅ ጠቢብ መሆን አይጠይቅም፡፡ በሌላው ውስጥ በቅዬ፣ ሌላውም በእኔ ውስጥ በቅሎ..ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ፈጥረናል፡፡ በባህልና በታሪክ፣ በወግና ልማድ ተወራርሰን የጋራ የሚል አብሮነትን አበጅተናል፡፡ዓ

ትውልድ የማኅበረሰብ መልክ ነው፡፡ ማኅበረሰብ የባህሉና የስርዐቱ ነጸብራቅ ነው፡፡ እኚህ ሁሉ ሀገር ወደምትባል የጋራ እውነት ይመሩናል፡፡ ሀገር ደግሞ ሁሉም በህልና ስርዐቶች በፍቅርና በአንድነት የሚከበሩባት የሁላችን ሰፊ ሜዳ ናት፡፡ ተጀምረን ያበቃንው በማኅበረሰብ ሥርት ውስጥ ነው፡፡ ለዚህ ማህበረሰብና ለስርዐቱ በጎ ማሳየት የወጣንበትን ከማክበር ጎን ለጎን ሀገር ማጽኚያ አውዳችንም ነው፡፡

የእኔ የአንተ የምንባባልባቸው የብቻ ታሪኮች አቆርቁዘውናል፡፡ ወኋላ ከመጎተትና ያሉንን የጋራ እሴቶች ከማደብዘዝ ባለፈ ጥቅም አልሰጡንም፡፡ አሁን የሌላውን የእኔ ብለን የምንነሳበትና ኢትዮጵያን በአዲስ ቀለምና ሸራ ላይ የምንስልበት ነው፡፡ ገባንም አልገባንም ሁላችንም አንድ ነን፡፡ አንዳችንም ብዙ ነን፡፡ እናም አብረን እናክብር..አብረን እንቁም፡፡

**በዓላት ትስስር መፍጠሪያ ገመዶች ናቸው። እንዳንላላ ሆነን የጠበቅነው፣ እንዳንወይብ ሆነን የጸናነው እንዲህ ባለው የጋራ ሥርዓት ነው**

# ስፖርት





## አዳጊዎቹ ክለቦች የመጀመሪያ የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታቸውን ዛሬ ያደርጋሉ

**ዓለማየሁ ግዛው**

የ2016 የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አዲሱን የውድድር ዓመት የመጀመሪያ ሳምንት ጨዋታዎች ባለፈው እሁድ በሁለት ጨዋታዎች መጀመሩ ይታወቃል፡፡ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጅማሬውን ባደረገው የአንደኛ ሳምንት መርሃ ግብር አዳማ ከተማን ከአዲስ አዳጊው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አገናኝቶ ያለምንም ግብ ሲጠናቀቅ፤ በቡና ደርቢ ኢትዮጵያ ቡና 1 ለምንም በሆነ ውጤት ሲዳማ ቡናን ማሸነፉ ይታወቃል፡፡ የሊጉ አንደኛ ሳምንት ቀሪ ጨዋታዎች ዛሬ ቀጥለው የሚካሄዱ ሲሆን፤ ወደ ሊጉ ያደጉት ሁለት ክለቦች የሚያደርጉት ጨዋታ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከወራት እረፍት በኋላ መስከረም 20/2016 ዓ.ም በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስታዲየም በደማቅ ሁኔታ ተጀምሯል፡፡ በመጀመሪያው ሳምንት ጨዋታዎች ቀዝቀዝ ብሎ ብዙ ግቦችን ሳያስተናግድ የተጀመረው ሊጉ ዛሬ በሚደረጉ ሁለት ጨዋታዎች አዲስ አዳጊዎቹን ክለቦች የሚያፋልም በመሆኑ በጉጉት ይጠበቃል፡፡ ሁለቱ ክለቦች በመጀመሪያ ጨዋታቸው የሚያገጥሟቸው ቡድኖችም ባለፈው ዓመት በሊጉ ግርጌ ያጠናቀቁ መሆናቸው ተመጣጣኝ ፉክክር ይኖራል ተብሎ ተገምቷል፡፡

ዛሬ 9 ሰዓት ላይ ፕሪሚየር ሊጉን ከ15 ዓመታት በኋላ ዳግም መቀላቀል የቻለው ሻሸመኔ ከተማ ከሊጉ ጠንካራ ክለብ ወላይታ ድቻ ጋር ይፋለማል፡፡ ሁለቱ ክለቦች የውድድር ዓመቱን በውጤት ታጅበው በመጀመርም የሊጉን ረጅም ጉዞ ከወዲሁ ለማሳመር የሚፋለሙ ይሆናል። በተለይ ለአዳጊዎቹ ክለቦች ከጨዋታው ውጤት ይዞ መውጣት በራስ መተማመናቸውንም ስለሚያጎለብት ለቀጣይ ጨዋታ ስንቅ ይሆናቸዋል። ቀድሞ ነጥብ መሰብሰብ ክለቦች በሊጉ የመቆየት እድላቸውን ስለሚያሰፋ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ጨዋታውን ማሸነፍ ለወላይታ ድቻ አስፈላጊ ቢሆንም ለሻሸመኔ ግን ከአስፈላጊም በላይ ነው፡፡

ሻሸመኔ ከተማ በከፍተኛ ሊጉ ያሳየውን አስደናቂ ብቃት ከደገመ ከዚህ ጨዋታ ነጥብ ይዞ መውጣት የሚችልበት እድል አለው፡፡ ይህ ግን ወላይታ ድቻ በሊጉ ካለው ልምድና ጥንካሬ አንጻር ለሻሸመኔ ከተማ ቀላል ላይሆን ይችላል። የጦና ንቦቹ በ2015 ዓ.ም የፕሪሚየር ሊግ ውድድር 12ኛ ደረጃን ይዘው ቢያጠናቅቁም በቀላሉ ከማይረቱ ክለቦች ይመደባሉ። አካላዊ ንኪኪዎችን በማብዛት የሚጫወቱ ስለሆነም ለተጋጣሚ ክለቦች በፈታኝነታቸው ይታወቃሉ። ሻሸመኔ በበኩሉ በከፍተኛ ሊጉ ጥሩ ጊዜን በማሳለፍ ሊጉን በአስደናቂ ሁኔታ መቀላቀሉ ይታወሳል፡፡ በተጨማሪም ከከፍተኛ ሊጉ ያሳደገውን አሰልጣኝ ውል ያራዘመ ሲሆን በዝውውሩም በርካታ ተጫዋቾችን በማስፈረም ራሱን ለማጠናከርም ችሏል፡፡ ይህም ያስፈረማቸው ተጫዋቾች ከአንድ ሙሉ ቡድን የሚበልጥ በመሆኑ ለቡድን ውህደት ጊዜ ስለሚያስፈልገው ጨዋታውን አስቸጋሪ ሊያደርግበት ይችላል፡፡ ሻሸመኔዎች በቀጣይ ጨዋታ ሀዋሳ ከተማን ሲያስተናግዱ የጦና ንቦች በበኩላቸው ከአዳማ ከተማ ጋር ይጫወታሉ፡፡



ሻሸመኔ ከተማ እና ሀምበሪቾ ዱራሜ የመጀመሪያ የፕሪሚየር ሊግ ጨዋታቸውን ከጠንካራ ክለቦች ጋር ያደርጋሉ፣

በከፍተኛ ሊጉ አስደናቂ ጊዜን በማሳለፍ ፕሪሚየር ሊጉን መቀላቀል የቻለው ሌላኛው ክለብ ሀምበሪቾ ዱራሜ ምሽት 12 ሰዓት ላይ ጨዋታውን ድሬዳዋ ከተማን በመግጠም ይጀምራል፡፡ ሀምበሪቾ በክረምቱ የዝውውር መስኮት ብዙም ተሳትፎ ያላደረገ ሲሆን ወደ ቅድመ ውድድር ዓመት ዝግጅትም የገባው ዘግየት ብሎ ነው። ክለቡ ራሱን በዝውውር በአግባቡ ባለማጠናከሩና በቂ የዝግጅት ጊዜን ባለማሳለፉ በሊጉ የሚኖረው ቆይታ ቀላል ይሆናል ተብሎ አይታሰብም። ተጋጣሚው ድሬዳዋ በበኩሉ የተሻለ ዝግጅትና የዝውውር ጊዜን በማሳለፉ ለሀምበሪቾ ከባድ ተጋጣሚ መሆኑ አይቀርም። የቡድኑን ወሳኝ አጥቂ ቢኒያም ጌታቸውን ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቢሸኝም ካለው የቡድን ጥልቀትና ልምድ አኳያ የአሸናፊነት ቅድመ ግምት እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ድሬዳዋ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሊጉ ለመቆየት የሚጫወት ክለብ እየሆነ መምጣቱ ለሀምበሪቾ የራስ መተማመኑን መጨመሩ አይቀርም፡፡ በዚህም በሁለቱ ክለቦች በኩል በጨዋታው ላይ ተመጣጣኝ ፉክክር እንደሚኖር ይገመታል፡፡

ድሬዳዋ በ2015 ዓ.ም በፕሪሚየር ሊግ 30 ጨዋታዎችን ከውኖ 11 ድል አድርጎ በ7 አቻ በመውጣት በ12 ደግሞ መሸነፉ የሚታወስ ነው፡፡ በዚህም 40 ነጥቦችን በመሰብሰብ 10ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር በሊጉ መቆየት የቻለው፡፡ ሀምበሪቾ በበኩሉ በከፍተኛ ሊጉ ከፍተኛ ተጋድሎን በማድረግ ነው ፕሪሚየር ሊጉን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀላቀለው፡፡ ክለቡ ወደ ፕሪሚየር ሊግ ያሳደገውን አሰልጣኝ ለተጨማሪ አንድ ዓመት የሚያቆየውን ውል ያስፈረመ ሲሆን ያም በክለቡ ውስጥ መረጋጋት የሚፈጥር በመሆኑ በሊጉ ጥሩ ተፎካካሪ ሆኖ እንዲቀርብ ያስችለዋል፡፡ በዚህ ጨዋታ ውጤት ይዞ መውጣት የሚችል ከሆነም በሊጉ የመቆየት ተስፋውን ከወዲሁ እንዲሰንቅ ያስችለዋል፡፡ ድሬዳዋ በሁለተኛ ሳምንት የሊጉ ጨዋታ ሊጉን በድል ከጀመረው ኢትዮጵያ ቡና ጋር ይጫወታል፤ ሀምበሪቾ ዱራሜ ደግሞ ከቻምፒዮኑ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይጋጠማል፡፡ ሁለቱም ክለቦች ከዚህ ጨዋታ ነጥብ ይዞ መውጣት ከፊታቸው ለሚጠብቃቸው ከባድ ጨዋታ መነቃቃትንና በራስ መተማመናቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዳቸውም ይሆናል፡፡


## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 036 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0004195297 ዘምዘም ኡስማን ያሲን ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የግዥ ደረሰኝ ቫት ከቁጥር 0050 እስከ 0070 የተሠራበት እና ከቁጥር 0071 እስከ 00100 ያልተሠራበት የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሠራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሠርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**ግብር ከፋይ ስም ዘምዘም ኡስማን ያሲን**

## ማስታወቂያ

ሜርሲ የንግድ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር በቤኒሻንጉል ክልላዊ መንግሥት ከማሽ ዞን ምዥጋ ወረዳ አይዣና ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ምርመራ ለማካሄድ በቀን 10/12/2015 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል፡፡
በመሆኑም በሚመለከተው ጂኦግራፊክ ኮኦርድኔት ክልል፣
1. $36^0$ 08’ 59. 116” E $09^0$ 08’ 32.89”N
2.36° 08’ 45. 935”E $09^0$ 08’ 33.572”N
3.$36^0$ 08’ 43. 932” E $09^0$ 08’ 39.793”N
4. 36° 08’ 45. 694”E $09^0$ 08’ 48.152” N ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለቢሮአችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን፡፡
ስልክ ቁጥር፡- 057 775 0715 057 775 0981 /057 775 0717 /ፋክስ fax 057 775 00 60
ፖ.ሣ.ቁ ጥር P.O.X Box 51
ማሳሰቢያ፡- መልሱን ሲጽፋልን የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ፡፡ Note : Please Quote our Ref.No. When Replying

**የቤ/ጉ/ክ/መንግሥት ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ**

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ ፀጋየ ኃ/ማርያም የሆነ ደረቅ ጭነት ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-27204 አማ ሊብሬ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ 15/12/2015 ዓ.ም በተፃፈ አመልክተዋል፡፡ ሊብሬውን ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ብቃት ማረ/ቡድን**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ተገኝ ጣሊሶ የተሽከርካሪ ዓይነት ሚኒባስ የሰሌዳ ቁጥር 3-90183 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር፡ LH113-6004685 የሞተር ቁጥር 3L-2160234 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ08/01/2016ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ይህንን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የቡራዩ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የባለንብረቱ ስም ደበበ አብዶ የተሽከርካሪው ዓይነት ት/ሳይክል የሰሌዳ ቁጥር 1-85820 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር፡EAYACARWALGO21380 ሞዴል TVS የሞተር ቁጥር፡AK4GL4706874 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ/ ጠፋብኝ ብለው በ01/13/15ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በቢሾፍቱ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ የዱከም ክ/ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ሐረሪ ክልል

በወ/ሮ ፈይዛ ሙስጠፋ ስም ተመዝግቦ ስለሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር 01-07601 ሐረ የሆነ ተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ በማንኛውም መልኩ ይዤዋለሁ የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ባያመለክቱ ምትክ ሊብሬ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት የትራንስፖርት ጽ/ቤት**
**ሐረር**